25 የስኬት ቁልፎች

በዶ/ር ኢዮብ ማሞ

Scanned with CamScanner

ማውጫ

1. ስኬት ከገንዘብ ይበልጣል /የእውነተኛ ስኬት ቁልፍ/ - 8
2. የትም የማይሄደው መርከብ /በአላማ የመኖር ቁልፍ/ - 15
3. ጫማ የሚያደርግ የለም /አጋጣሚን የመጠቀም ቁልፍ/ - 21
4. ጨምዳዳው መቶ ብር /ማንነትን የመቀበል ቁልፍ/ - 27
5. መራራው ሂትለር /ካለፈው ታሪክ የመፋታት ቁልፍ/ - 33
6. ታላላቅ ሰዎች አይወለዱም! /የምርጫ ቁልፍ/ - 39
7. "ውስንነቴ ላይ አተኩሬ አላውቅም" /ብርታት ላይ የማተኮር ቁልፍ/ - 45
8. የነፋሱ ግፊያ ወደ ከፍታዬ ያወጣኛል /ተግዳሮትን ለአላማ የመጠቀም ቁልፍ/ - 51
9. ሞት ነጋዴው ሞተ /የዘላቂነት አመለካከት ቁልፍ/ - 57
10. እንዳያይ ሳይሆን እንዳያተኩር /የትኩረት ቁልፍ/ - 63
11. አንድ ቀን በጨረቃ ላይ እራመዳለሁ /የራእይ ቁልፍ/ - 69
12. ቴርሞሜትር ነህ ወይስ ቴርሞስታት? /ነገሮችን ወደመኖር የማምጣት ቁልፍ/ - 75
13. ኤቨረስት ሆይ፣ አሸንፍሃለሁ /ራስን የማሻሻል ቁልፍ/ - 81
14. የውሻዬና የመኪናው ነገር /የሚፈልጉትን የማወቅ ቁልፍ/ - 87
15. ለትምህርት የሆነ ስህተት /ስህተትን ለትምህርት የመለወጥ ቁልፍ/ - 93
16. በ30 ዓመቱ ሞተ፣ በ60 ዓመቱ ተቀበረ /በአላማ የመጽናት ቁልፍ/ - 99
17. የሚጀመሩ፣ ነገር ግን የማይጨረሱ /ጀምሮ የመጨረስ ቁልፍ/ - 105

18. የትኛውም መንገድ ይወስድሃል /ግብን የማውጣት ቁልፍ/ - 111
19. ወሬው ሁሉ የመውጊያ ፍርሃት ነበር /ፍርሃትን የማሸነፍ ቁልፍ/ - 117
20. ስለ ተፈተንክ ሳይሆን ስለተዘጋጀህ /የመዘጋጀት ቁልፍ/ - 123
21. ቢዚ ነኝ ተወኝ! /የጊዜ አጠቃቀም ቁልፍ/ - 129
22. ሬጣሪ ሆይ፣ ወደ እኔነቴ መልሰኝ /ራስን የመሆን ቁልፍ/ - 135
23. አእምሮዬን ለምን አጨናንቀዋለሁ? /የተግባራዊ እውቀት ቁልፍ/ - 141
24. የታሰረው እግሩ ሳይሆን ጭንቅላቱ ነው /የአመለካከት ቁልፍ/ - 147
25. በጽኑ ከፈለከው ታገኘዋለህ /በጽኑ የመፈለግ ቁልፍ/ - 153

Scanned with CamScanner

መግቢያ

ስኬትን የማይመኝ ማን አለ? ለስኬት የሚሰጠው ስእልና ትርጉም ይለያይ እንጂ ስኬትን የመፈለግን ጎዳና ያልተያያዘ ሰው በዚህች ዓለም ላይ ተፈልጎ አይገኝም:: የስኬት ጥማት ባይኖር መጓጓትና መነሳሳት የተሰኙ አስገራሚ ስሜቶች ትርጉም ያጣሉ:: የምንጓጓውና የምንነሳሳው ለምንድን ነው? ስኬት ነው ብለን ወዳሰብነው ደረጃ ለመድረስ አይደለምን? በተቃራኒውም፣ እንደ ተስፋ መቁረጥ፣ ጭንቀትና ኃዘን የመሳሰሉትም የጠንካራ አሉታዊ ስሜቶቻችን ከስኬት ጋር የተያያዙ ናቸው:: ተስፋ መቁረጥ የሚባለው ስሜት እንዲኖር በቅድሚያ ተስፋ ያደረግነው ነገር ሊኖር የግድ ነው:: ተስፋ የተደረገውን ነገር አጓጊነት የወሰነው ለመድረስ የቃጣንለት ነገር እንደ ስኬት ስለሚቆጠር ነው::

የስኬት ጥማት ከጽንስ እስከ ሽምግልና የሚከተል በሰው ማንነት ውስጥ የተፈጠረ እውነታ ነው::በማህጸን ውስጥ ላለ ሕጻን ከዚያ እትብት ተላቅቆ መውጣት ታላቅ ስኬት ነው:: የተወለደው ደግሞ አልቅሶ የእናቱን ጡት በአፉ የማስገባቱ፣ በጀርባው ከተንጋለለበት ቀና ብሎ ዳዴ ወደማለት መሸገሩ፣ በእግሩ የመቆሙና "ወፌ ቆመች" ሲባል በፈገግታ መሞላቱ፣ መራመዱና ወደመሮጥ መዝለቁ ሁሉ የስኬት ጥማቱን ሊያረኩለት እየተቀባበሉ ያሳድጉታል::

ሕጻኑ እያደገ ሲሄድ መጫወቻን ወደ እጁ ከማስገባት ጀምሮ በትምህርት ውጤት ልቆ እስከመገኘት ድረስ የወጣትነቱን የስኬት ጥማት ያሰፋል:: ለሰጠው የፍቅር ጥያቄ የእሺታ መልስ ማግኘቱ፣ በትምህርት የመግፋቱና የመመረቁ ጎዳና ሌላው ስኬት መመዘኛ ደረጃ ሆኖና ተራውን ጠብቆ ይመጣል:: የወጣለት ሰርግ፣ የቀናለት ኑሮ፣ ያማሩ ልጆች፣ ልጆች ተምረው፣ ተመርቀውና ቤትን መስርተው የመኖራቸው ጉዳይ እንደ አንድ ነገር ይቀባበሉናል:: እነዚህ ሁኔታዎች ሰመሩም አልሰመሩም፣ የመጨረሻው

አድሜአችንን በሰው እጅ ላይ ሳንወድቅና እድሜ ጠግበን የማለፋችንም ነገር የሁላችን የስኬት ጉጉት እጣ ነው::

እውነታውን አምነህ ተቀበለው! የስኬት ባሪያ ነህ - የምትኖረው ለስኬት ነውና:: ሰው ስኬት ነው ብሎ ያመነበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ዋጋን ይከፍላል:: ጊዜውን፣ ገንዘቡን፣ ጤናውን፣ ጓደኝነቱን፣ አንዳንዱም ትዳሩን እስከመከፈል ይቃጣዋል- ለስኬት!

እውነተኛ ስኬት ግን ምንድን ነው? እንዴትስ እዚያ ደረጃ ላይ ይደረሳል? በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ የተለያዩ የስኬት ቁልፎችን እንመለከታለን:: አንባቢዬ እነዚህን ቁልፎች በተከፈተ ልቦና በማጤን እንዲጠቀምባቸውና አንድ እርምጃ ወደ ፊት ለመሄድ እንዲወስን አበረታታለሁ::

መልካም ንባብ!

Scanned with CamScanner

1

ስኬት ከገንዘብ ይበልጣል

የእውነተኛ ስኬት ቁልፍ

ስኬት የሞላበት ሕይወት ምንድን ነው? ለስፖርት አፍቃሪ ስኬት በአንድ ስፖርት ታዋቂ መሆን ነው። ለውበት አድናቂ ስኬት በሰው ሁሉ መወደድና መደነቅ ነው። ዝናን ለሚወድድ ሰው ዝነኛነት ከስኬት ጋር ይገናኝበታል። ስልጣን ወዳድ፣ ባለበት ተቋምም ሆነ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ ማግኘት ስኬቱ ነው። ከእነዚህ ሁሉ ይልቅ ግን በብዙዎች ሃሳብ ውስጥ ስኬት ከሃብትና ከብልጽግና ጋር ግንኙነት አለው። በሌላ አባባል፣ ሰው ሁሉ፣ "ስኬታማነት ማለት ይህ ነው" ብሎ የሚያስበውን ነገር በገንዘብ ከመበልጸግ ጋር ማገናኘቱ አይቀርም። ስለዚህም፣ ስኬት ማለት ሃብታም መሆን ነው ብሎ የማያስብ ሰው ካለ ይገርማል።

ዶ/ር ጃን ማክስዌል Your Road Map for Success በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ አንድ አስተማሪ ታሪክ አስፍረዋል። በ1923 ሺካጎ በምትባል የአሜሪካ ከተማ ውስጥ ሰባት የሚሆኑ በአለም ቀደምተኝነትን የያዙ የአገሪቱ ሃብታሞች ተሰብስበው ነበር ይባላል - ስለስኬትና ስለሃብት ለመወያየት። የእነዚህ ሰባት ባለሃብቶች ጥርቅም ሃብታቸው የአሜሪካንን የአገር ውስጠገቢ በጀት ይበልጥ እንደ ነበርም ይነገራል።

እነዚህ ሰዎች በብዙዎች ሰዎች እንደበት የተሳካላቸው የተሰኙ ነበሩ:: ፍጻሜአቸው ግን እንዲህ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል:-

ቻርልስ ሽዋብ (Charles Schwab – president of the largest independent still company) - በድህነት፣ በከስረትና በታላቅ ኃዘን ሞተ::

አርተር ኩተን (Arthur Cutten – greatest of the wheat speculetors) - ከአገሩ ውጪ በእዳ ተጠላልፎና ከስሮ ሞተ::

ሪቻርድ ዊትኒ (Richard Witney – president of the New York Stock Exchange) - በኒው ዮርክ ከሚገኘው ሲንግ ሲንግ ከተሰኘው እስር ቤት ማቅቆ ልክ ሲፈታ ሞተ::

አልበርት ፎል (Albert Fall – member of a U.S. president's cabinet) - ከእስር ቤት በይቅርታ ተፈትቶ አቤቱ ሞተ::

ጄሲ ሊቨርሞር (Jess Livermore – greatest "bear" on Wall Street) - ራሱን አጥፍቶ ሞተ::

ሊዎን ፍሬዠር (Leon Fraser – president of the Bank of International Settlement) - ራሱን አጥፍቶ ሞተ::

ኢቫር ክሩገር (Ivar Kreuger – head of the world's greatest monopoly) - ራሱን አጥፍቶ ሞተ::

"የተወሰነ ደረጃ ከደረስኩ በኋላ የገባኝ ይህ ነው፤ ገንዘብ ዋጋ ቢስ ነው:: ስኬት ከገንዘብ ይበልጣል" – (Aristotle Onassis – Greece Millionaire)

ብዙ የገንዘብ ባለጠጎች በብዙ ሚልየን የሚቆጠር ብርን አካብተው እንኳ ስኬትን አሁንም በብርቱ ሲፈልጓት ይታያሉ:: ስለዚህም ብዙዎች ይህንን እውነት ወደ ማመን መጥተዋል - የብር ብልጥግና ብቻውን ስኬት ማለት አይደለም:: ሃብት ከስኬት ጋር የማይገናኝበት ብዙ ምክንያቶች አሉ:: ለምሳሌ፣ ቀደም ብለን እንዳየነው፣ በብዙ ሃብት የተሞሉ ሰዎች መጨረሻቸው አሳዛኝ እንደሆነ ስንመለከት ስኬትን ከተለየ እይታ እንድንመለከተው እንገደዳለን:: በተቃራኒው፣ ምንም ያህል በሰው እይታ የሚሞላ ንብረት ሳይኖራቸው የሰላምና ለሰው የሚተርፍ ሕይወት ጠግበው የሚኖሩና ኖረውም በክብር የሞቱ ሰዎች ቁጥር እጅግ ብዙ መሆኑ አሁንም ለስኬት ያለንን እይታ እንድንጠይቅ ይጋብዘናል:: በገንዘብ መበልጸግ ከስኬት ክፍል እንደ አንዱ ሊቆጠር ይችላል እንጂ የስኬት ጥጉ አይደለም:: የገንዘብ ብልጽግና ከሌሎች የስኬት "ንጥረ ነገሮች" ጋር ተዳብሎ ሲገኝ ብቻ ነው ስኬት ሊባል የሚችለው::

ለምሳሌ:- በሰሜን አሜሪካ በተደረገው ጥናት 80 በመቶ የሚሆኑ የሎተሪ አሸናፊዎች በአምስት አመት ውስጥ ራሳቸውን በከስረት ውስጥ እንደሚያገኙትና እንዲያውም አንዳንዶቹ የጎዳና ተዳዳሪዎች እስከመሆን እንደሚዘቅጡ መረጃ ያሳያል:: እነዚህ ሰዎች በእጃቸው በድንገት የገባውን ሃብት የሚመጥን ስኬታማ አመለካከት ቀድሞውኑ ስላልነበራቸው ተመልሰው ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ያዘቅጣሉ፣ አንድ አንዴም ከዛ ወደ ወረደ ሁኔታ! አየህ፣ ገንዘብ ስኬታማነትን አያመጣም፣ ስኬታማነት ግን የገንዘብን ብልጽግና ሊያመጣ ይችላል::

ልንዘነጋው የማይገባን አንድ እውነት አለ፤ አንዳንድ ሰዎች ባላቸው ስኬታማ አመለካከትና የሕይወት ጥራት በገንዘብ ወደ መበልጸግ ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ:: ወደዚህ ብልጽግና እንዲደርሱ ያበቃቸው ስኬታማ አመለካከትና ማንነት ያንን በእጃቸው የገባውን ሃብት በቅጡ መያዝ፣ ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስና ለብዙዎች ጥቅም እንዲውል የማድረግ ብቃቱም እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል::

በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ሰዎች በድንገት እጃቸው በገባው ገንዘብ ምክንያት ወይም ደግሞ የተለያዩ ተንኮል የሞላባቸውን መንገዶች በመጠቀም ሃብት እጃቸው ይገባና ይበለጽጋሉ:: ሆኖም፣ ቀድሞውኑ ብልጽግናውን ወደ መኖር የሚያመጣ ማንነት ስላልነበራቸው ብልጽግናውን የመጠበቅም ማንነት ማምጣት ይሳናቸዋል:: ውጤቱ - ለሰላም ሊሆን የሚገባው ለጭንቀት፤ ለእድገት ሊሆን የሚገባው ለውድቀት!

"ስኬት ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ ብዙ አዋቂዎች የሚሰጧቸውን መልሶች ስንጨምቃቸው የሚከተሉትን እውነታዎች እናገኛለን::

ማንነትንና ብቃትን ማወቅ

አንድ ሰው ማንነቱን በቅጡ ሲያውቅና በዚህ ዓለም ላይ በሕይወት የሚኖርበትን ዘመን ምን አከናውኖ ማለፍ እንዳለበት ሲገባው የስኬት መስመር ውስጥ የገባ ሰው እንደሆነ ግልጽ ነው:: ደካማውንና ብርቱ ጎኑን፣ የሚያጓጓውንና የማያጓጓውን፣ የሚሳካለትንና የማይሳካለትን ማወቅ ያረፈና የተሳካለት ሕይወት ከመኖር ጋር በቀጥተኛ መንገድ የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው:: ማንነትህን በሚገባ ወደ ማወቅ ስትመጣ ጊዜህንና ጉልበትህን በምን ላይና በምን መልኩ ማሳለፍ እንዳለብህ ጥርት ባለ መልኩ ታውቃለህ:: ከሌሎች ሰዎች ተለይተህ መኖርና ማደግ ትችላለህ፤ ከራስህ ተለይተህ ግን መኖርም ሆነ ማደግ አትችልም:: ስለዚህ ይህንን በፍጹም ልትለየው የማትችለውን አጋር በሚገባ እወቀው:: ማንነትህን በቅጡ ስታውቀው የሚሳካልህ ላይ በማተኮርና የማይሳካልህን ተወት በማድረግ ከስኬት ወደ ስኬት ትዘልቃለህ::

"ሁሉም ሰው ብልህ ነው:: ነገር ግን፣ አሳን ዛፍ ላይ በመውጣት ችሎታው ብቃቱን ከመዘንከው ይህ አሳ እድሜውን በሙሉ ደደብ ነኝ ብሎ በማመን ይኖራል" – Albert Einstein

አንተ ውስጥ አስገራሚ ብቃትና የእውቀት ዝንባሌ አለ፤ በውስጥህ የስኬት ዘር አለ፣ ለመሆንና ልትችለው የተፈጠርክለትን ማንነት! ይህንን ችላ ብለህ ለአንተ ያልተሰጠውን ማንነት ሆኖ ለመገኘትና ከሆንከው ማንነትህ ጋር የማይፈስሰውን ለማወቅና ለማድረግ መሞከር ማለቂያ የሌለው ጉዞ ይሆንብሃል::

በአንዳንድ በዚህ ግንዛቤ ባልበሰሉ የትምህርት ተቋሞች አካባቢ ተማሪ ማንነቱን ተከትሎ እንዲማር የሚፈቅድ አሰራር የለም:: ለምሳሌ፣ የእጅ ሙያ ዝንባሌ ያለውን ተማሪ የሚሳካለት አንብቦ ሲሸመድድ ብቻ እንደሆነ ጫና ስናደርግበትና ተማሪው የማይችለውን ጭነት ስንጭንበት ያለማወቅን ስሜት እንጨምርበታለን:: ስኬት ግን የሚመጣው ማንነትህንና ዝንባሌህን በማወቅና በዚያም ላይ በመገስገስ ነው::

እምቅ ብቃትህን መፍታት

በአንድ የትም ማደግ በማይቻልበት ውስን አካባቢ ተወልዶና ከእርሱ በፊት በዚያው ስፍራ ተወልደው ያደጉ ሰዎች የትም እንዳልሄዱ ያየ ልጅ ከዚያ ስፍራ የመውጣት እድልን አግኝቶ ውስጡ ያለው እምቅ ማንነት ቀዳዳ ሲያገኝ የሚደርስበት ደረጃ አስገራሚ ነው:: ይህ እውነታ አንድ ሰው የተመቻቸ ሁኔታ ካገኘ ሊደርስ የሚችልበት ከፍታ እጅግ የላቀ መሆኑን አመልካች ነው:: ይህ እንዲሆን ውስጥህን የሚፈታውን ነገር ማድረግ የግድ ነው:: አንተ ውስጥ ገና ያልወጣ እምቅ ብቃት አለ:: ይህ ብቃት የሚገኘው በአንተ ውስጥ ብቻ ነው:: አወላለድህ፣ አስተዳደግህ፣ ምኞትህ፣ ማድረግ የምትችለውና የምታልፍበት ሁኔታ ሲደመሩ አንተን ብቸኛ ያደርጉሃል - እንዴት ያለ ሃብት! ስኬት ማለት ይህ ነው - መሆን የምትችለውን ለመሆን መነሳት፣ ውስጥህ ያለውን ውብ ነገር መፍታትና መሄድ የምትችለውን ያህል መሄድ!

"ሰውን አሁን ካለበት ሁኔታ አንጻር ስናስተናግደው፣ ካለበት ሁኔታ የበለጠ እናወርደዋለን:: ያለውን እምቅ ብቃትና ወደ ፊት መሆን የሚችለውን አይተን እንደዚያ

ስናስተናግደው፣ መሆን የሚገባውን እንዲሆን መንገድ እንከፍትለታለን" – Johann Wolfgang Von Goethe

ራስህን አሁን ካለህበት ሁኔታ ባሻገር ማየት ካልጀመርክ በሁኔታህ እንደታሰርክ ትኖራለህ:: ራስህን ማየት የሚገባህ መሆን ከምትችለውና ከታመቀው ብቃትህ አንጻር ነው:: ይህንን ብቃትህን ለማወቅ ከፈለግህ፣ ያለመርካት ስሜቶችህን አዳምጣቸው:: በተጨማሪም ከዚህ የተሻለ ማድረግ ይቻላል ብለህ የምታስባቸውን ጉዳዮች አጢናቸው - ታገኘዋለህ! አሁን ካለህበት ሁኔታና ከምትሄድበት አቅጣጫ የተሻለ ነገር እንዳለና አንድ ቀን እዚያ ደረጃ መድረስ እንዳለብህ ውስጥህ ከናፈቀ፣ የእምቅ ብቃትህን ቁልፍ አግኝተኸዋል::

ለሌሎች የሚተርፍን ዘር መዝራት

ብልጽግና፣ ሃብት፣ እውቀት፣ ዝናና ኃይል ለሌሎች ካሉበት መነሳት ላቃታቸው ሰዎች ጥቅም እስኪውል ድረስ ከስኬት ጋር በፍጹም ሊያያዝ አይችልም:: ለሌሎች የመትረፍህን መጠን ለማወቅ፣ ወደ እጅህ በገባውና ከእጅ በወጣው መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከት:: የገባው ብዙ፣ ለሌሎች ጥቅም የወጣው ግን ጥቂት ከሆነ ከስኬት ጎዳና ውጪ ነህ:: አንተ የደረስከበት ደረጃ የደረስከውና ያገኘኸውን መልካም ነገር ያገኘኸው በሰው በኩል መሆኑን አትዘንጋ - ከመወለድና ለመራመድ ከመብቃት ጀምሮ! አንተ ካለፍክ በኋላ አሻራህ የሚገኝበት ነገር ስራ:: አንተ በፍጹም ልትጠለልበት የማትችለውን ዛፍ ትከል::

"ታላቅነት ማለት አንተ ካለፍክ በኋላ ለሌሎች እልፎ የሚሄድና የሚዘልቅን ነገር ጀምሮ ማለፍ ማለት ነው" – William James

ይህንን አትዘንጋ - በምታገኘው ነገር ትኖራለህ፣ በምትሰጠው ነገር ሌላውን ታኖራለህ:: ስኬት ማለት ይህ ነውና! እውቀትህና ሃብትህ፣ ብርታትህና በእጅህ የገባው ሁሉ ከአንተ

Scanned with CamScanner

አልፎ ለሌላው ሲፈስስ ወደስኬት ጥግ በመድረስ ላይ ነህ:: ለራስ በልቶ መኖርና መሞት የታናሽነት ሁሉ ታናሽነት ነው:: ታላላቆች ከእነሱ ለሚበልጥና ለሌላው ለሚተርፍ ነገር የሚኖሩና የሚሰሩ ናቸው::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የእውነተኛ ስኬት ቁልፎች:-

1. ማንነትንና ብቃትን ማወቅ
2. እምቅ ብቃትህን መፍታት
3. ለሌሎች የሚተርፍን ዘር መዝራት

የገንዘብ ብልጽግና ከሌሎች የስኬት "ንጥረ ነገሮች" ጋር ተዳብሎ ሲገኝ ብቻ ነው ስኬት ሊባል የሚችለው::

2

የትም የማይሄደው መርከብ

በአላማ የመኖር ቁልፍ

ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ምንድን ነው? በሁለት እግሩ መሄዱ ነው? መነጋገር መቻሉ ነው? ወይስ ... ? ሰው ከእንስሳ የሚለይባቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ ዋነኛው መለዮ ግን ሰው በዓላማና በእቅድ ለመኖር የመቻሉ ብቃት ነው:: መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መነሳት፣ መጫወትና ወዲህና ወዲያ ማለት ለእንስሶችም የተሰጠ ነገር ነው:: በእነዚህ ተግባሮች ውስጥ ዓላማ ሲካተትባቸው ብቻ ሰው በእውነትም ሰው ወደ መሆን ይመጣል:: ዓላማ የለሽ ኑሮ የሚኖር ሰው፣ ሰው ሆኖ ከሰውነት በታች እንዲኖር ይገደዳል::

በአንድ ከተማ ውስጥ በየምሽቱ ሰዎችን እየጫነ ለሰዓታት በባህሩ ላይ ወዲህና ወዲያ በመሄድ ካሳለፈ በኋላ በመጨረሻ ሰዎቹን የነበሩበት ስፍራ መልሶ የሚያራግፋቸው መርከብ እንዳለ ይነገራል:: ይህ ግዙፍ መርከብ በውስጡ አለ የተባለ በማንኛውም ዘመናዊ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን አካቷል:: መዝናኛው፣ መዋኛው፣ መጫወቻው፣ የሚበላውና የሚጠጣው ሙሉ ነው! የዚህ መርከብ ስም፣ "የትም የማይሄደው መርከብ" በመባል ይታወቃል:: ይህ መርከብ በየምሽቱ ሰዎችን በመጫን ወዲህና ወዲያ ይሄዳል፣ ነገር ግን የትም አይደርስም:: በጉዞው ወቅት ተሳፋሪዎቹ ይጫወታሉ፣

Scanned with CamScanner

ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይደንሳሉ፣ ይተዋወቃሉ፣ ያወራሉ ... በመጨረሻ ግን ራሳቸውን የተነሱበት ቦታ ላይ ያገኙታል:: በእለቱ በተከናወነው ነገር "እጅግ ደስ ከተሰኙ" በኋላ ሌላ የደስታ ምንጭ ፍለጋ ወደየስፍራቸው ይሰማራሉ - ጉዞአቸው ግን የትም አልወሰዳቸውም!

"ታላላቅ አእምሮዎች ዓላማ አላቸው፣ ሌሎቹ ግን ምኞት ብቻ ይዘዋል" - Washington Irving

በዚህች ምድር ላይ ከ7 ቢልየን ሕዝብ በላይ ወዲህና ወዲያ ሲመላለስና ዓለም ሕይወት ባላቸው ፍጡራን መሞላቷን ማየት ደስ ያሰኛል:: ሆኖም ይህንን ደስ የሚያሰኝ ነገር ጥቁር ነጥብ የሚጥልበት አንድ አሳዛኝ ነገር አለ፣ ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች የሚሄዱበትን አያውቁም:: እነዚህ ሰዎች በቀን ውስጥ ብዙ እንቅስቃሴ ቢያስመዘግቡም፣ የእነዚህ እንቅስቃሴዎች ድምር ውጤቱ ዜሮ ወይም ባዶ ነው::

የብዙ ቁጥሮች ድምር ዜሮ የሚሆነው እንዴት ነው? መልሱ ቀላል ነው:: የብዙ ቁጥሮች ድምር ዜሮ የሚሆነው የተደመሩት ቁጥሮች በሙሉ ዜሮ ሲሆኑ ነው:: የየእለት እንቅስቃሴአችን ዜሮ የሚሆንበት ብቸኛ ምክንያት ካለምንም ዘላቂ እይታ ስለምንተገብረው ነው:: የእለቱ ተግዳሮት የሚያመጣብን ትግልና የጊዜው መልካም ገጠመኝ የሚሰጠን ጊዜአዊ ደስታ ልንገነባው ከሚገባን አጠቃላይ የሕይወት ዓላማ አይነ-ህሊናችንን ይጋርዱታል:: ግንባታ-የለሽ ደስታ፣ ግንባታ-የለሽ ጨዋታ፣ ግንባታ-የለሽ ስራ፣ ግንባታ-የለሽ ወዳጅነት፣ ፍጻሜ የለሽ ሩጫ ... ዝርዝሩ ብዙ ነው:: አንድ ሰው ስኬታማነትን በብርቱ ከፈለገ፣ በሕይወቱ ያለው ዓላማ ጉዳይ ግድ ሊለው ይገባል::

ዓላማ ከሌለው ሩጫ ለመዳን፣ ትርጉም የሞላው ሕይወት ለመኖርና ራስን መስመር ለማስያዝ የሚከተሉትን ምክሮች እለግሳለሁ::

አእምሮህን ተጠቀም

በዚህ ዓለም ላይ የተፈለሰፉትን አስገራሚ ግኝቶች አስብ:: የሰው ዘር የማሰብ ብቃቱን ተጠቅሞ የደረሰበትን ደረጃ ተመልከት:: ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ ጥናቶች እንደሚነግሩን አእምሮአችንን ካለው ብቃት አስር በመቶውን ብቻ ነው የምንጠቀመው:: የቀረውን ዘጠና በመቶ የአእምሮአችንን ብቃት መጠቀም ብንችል ምን ማድረግ እንችላለን? ይህ እውነታ፣ ከዚህ በፊት አግኝተህ ከምትለው ውጤት በብዙ እጥፍ ልታገኝ የምትችልበት ብቃት እንዳለህ አመልካች ነው:: ሰዎች ወደ ትምህርት ቤት ሄደው ገንዘባቸውን የሚከፍሉትና ጊዜአቸውን የሚሰውት ይህንኑ አእምሮ የተባለውን ሞተር ለመቀስቀስና ለማንሳሳት መሆኑን አትርሳ:: ማሰብ ትችላለህ፤ መሻሻል ትችላለህ፤ ማቀድ ትችላለህ፤ አዳዲስ ነገሮችን መፍጠር ትችላለህ!!! ቁልፉ አንተው ጋር ነው ያለው:: ይህ ቁልፍ ውሳኔ ይባላል:: በከንቱ የምታሳልፋቸውን ጊዜአቶችህን እንደገና በማደስ አእምሮህን በመጠቀምና በማሰብ አዲስ ንድፍ ማውጣት ትችላለህ::

"ቀድሞውኑ የሕይወታችን ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት የሆነንን ያንኑ አስተሳሰባችንን ተጠቅመን ለእነዚያው ችግሮች መፍትሄ ልናገኝላቸው አንችልም" – Albert Einstein

አሁን የምንኖረውን ኑሮ የወሰነልን ያለፈው አስተሳሰባችንና ውሳኔአችን እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: አእምሮአችንን የለጠጥነውንና ለማሰብ የተነሳነውን ያህል ሕይወታችንም በዚያው ልክ ይነሳል:: ይህ እንዲሆን አሁን ያለንበትን ሁኔታና ኑሮ ወደ መኖር ያመጣውን አመለካከትና ያለፈ ታሪክ ለመቀየር እንደገና ቆም ብለን ማሰብ አስፈላጊ ነው:: የምናስባቸው ሃሳቦች ወሳኞች ናቸው:: ዓላማ ያለው ሕይወት ለመኖር አእምሮን መጠቀም የግድ ነው - ሕይወት የአስተሳሰብ ጥርቅም ናትና:: ሳናስብ ማሰላሰል አንችልም፤ ሳናሰላስል ደግሞ አንድ እውነታ ጥግ ላይ መድረስ አስቸጋሪ ነው:: የነገሮችን ግራና ቀኝ አይተንና ከዚህ የተሻለ መንገድ እንዳለ አምነን ለላቀ እይታ ስንነሳ የዓላማን ጎዳና እናገኘዋለን::

Scanned with CamScanner

በየቀኑ ገጠመኝህና በስሜትህ አትነዳ

አንዳንድ ሰዎች የተከፈተ በር ስላገኙ ብቻ ካለምንም ጥያቄ ሰተት ብለው ይገባሉ:: ስራን በጋራ እንስራ የሚላቸው ሰው ስለተገኘ ብቻ ውል ለመፈራረም እጅግ ይቸኩላሉ:: ለመጣላቸው ገጠመኝና እድል ምንም ጥያቄ ሳያነሱ ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ:: ሌሎች ደግሞ ጥሩ ስሜት እስከሰጣቸው ድረስ አንድን ነገር ከማድረግ አይመለሱም:: በእለቱ የሚከተሉት ነገር ለስሜታቸው ጥሩ መነቃቃት የሰጣቸውን ሁኔታ ነው:: እስቲ ቆም በልና በጣም የምትወዳቸውን የምግብ አይነቶች ቁጠራቸው:: ከእነዚህ ምግቦች መካከል አብዛኛዎቹ ለምላስ የሚጥሙ፣ ለጤንነት ግን ጠንቅ የሆኑ ናቸው ብዬ አገምታለሁ:: በስኳር የተለወሰውና ጣፋጩ፣ በዘይት የተጠበሰው፣ ቅባት የበዛበትና በኬሚካል ተቀምሞ የቆየው ብሉኝ ብሉኝ የሚል ስሜትን ያነሳሳል:: እንግዲህ፣ አስተዋይ ሰው ከሆንክ አንድን ነገር የምታደርገው ስለጣፈጠህ ወይም እድል ስለተገኘ ሳይሆን በነገሩ ትክክለኛነት ስላመንክበት ብቻ ነው:: አንድ ነገር የምታደርገው ለስሜትህ ስለተስማማህ ብቻ ሳይሆን ከአላማህ አንጻር ትክክለኛ ነገር ስለሆነ መሆን አለበት:: ይህ የስኬታማ ሰዎች መለዮ ነው::

“ገጠመኞች እንዲገዙን መፍቀድ እንችላለን፣ ወይም ደግሞ በውስጣችን ባለን አመለካከት ገጠመኞችን በቁጥጥር ስር ማዋል እንችላለን” – Earl Nightingale

ብዙ ሰዎች የገጠመኝ ባሪያዎች ሆነው ይኖራሉ:: ሕይወታቸውን የሚመሩት እነሱ አይደሉም፣ የእለቱ ገጠመኝ እንጂ! ከአንድ ስፍራ ተነስተው ሌላኛው ስፍራ ላላቸው አስፈላጊ ቀጠሮ እስኪደርሱ ድረስ በመካከሉ የሚቀርብላቸውን ግብዣ ሁሉ ያስተናግዳሉ:: “እምቢ” የሚሉት ነገር የላቸውም:: ይህ “ቀውጢ” ሕይወት ነው፣ የትም አያደርስም:: ስኬታማ ሰው የጀመረውን ነገር ጥግ እስከሚያደርስ ድረስ ስሜትንና ገጠመኝን ወደ ጎን ያስቀምጣቸዋል፤ ጉዞውንም ከዓላማው አንጻር ይቃኛል:: አንተም የስሜትና የገጠመኝ ባሪያ ላለመሆን ዛሬውኑ መወሰን አለብህ:: ይህንን ማድረግ ቀላል

ሆኖ አይደለም፣ መደረግ ያለበት ነገር ስለሆነ ነው:: የሕብረተሰባችን የባህል ቅኝት በብዙ ሺህ አመታት የተከመሩ ዓላማ-መር ሕይወት መኖር የማይቻልባቸውን እንቅፋቶች በየቀኑ በፊትህ ይደነቅራል:: ከአንዳንድ የባህል ልምምዶች ጋር መጻረርና ብዙሃኑን ማስቀየም የሚያጓጓ ምርጫ ባይሆንም እንኳ ብልሃት ተፈልጎለት ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ነው:: ከዚህ ውጪ ሕይወት የለምና::

ተግባሮችህን ከዓላማህ አንጻር ቃኛቸው

ውሎህ፣ ጓደኝነትህ፣ የምትማረው ትምህርት፣ የምታነባቸው መጻህፍትና የመሳሰሉት ሁኔታዎች በመላ ምትና በአቦሰጡኝ ሳይሆን ከአላማህ አንጻር ሊመረጡ ይገባቸዋል:: አንድ ሰው ሃኪም የመሆን ሕልም እያለው ጊዜውን ሁሉ ከዚያ ጋር የማይዛመድን መጻህፍትን እያነበበ ካሳለፈ አንድ የተበላሸ ነገር እንዳለ ያሳያል:: ይህ ሰው መጀመሪያውኑ ህክምናን የመረጠው በስህተት ወይም በሰው ግፊት ነው፣ አለዚያም “የተግባርና የውጤት” ህግ በቅጡ አልገባውም:: ከላይ እንደገለጽኩት፣ የምትይዛቸው ጓደኞች፣ የምታሳልፍባቸው ቦታዎች፣ የምታነባቸው መጻህፍትም ሆኑ የምትከታተላቸው ግኝቶች ከዝንባሌህና ከዓላማህ አንጻር ሲሆኑ ስኬት የአጋጣሚና የእድል ጉዳይ መሆኑ ይቀርና የእርግጠኝነት ጉዳይ ይሆናል::

“የየእለት ተግባራችን በሕይወታችን ቀዳሚነት የሰጠነውን ነገር ጠቋሚ ነው”– Mohandas Gandhi

በየእለቱ ለመተግበር የምትነሳሳለትን ነገር አስተውለው:: ብዙውን ጊዜህን የምታሳልፈው ምን ነገር ላይ እንደሆነ እስቲ በሚገባ ተመልከት:: በእጅህ የሚገባውን ገንዘብ አብዛኛውን በምን ላይ እንደምታውለው መለስ ብለህ በጥንቃቄ አስላው:: ሃሳብህንም የጣልከባቸውን ሁኔታዎች እስቲ አጢናቸው:: እነዚህ ሁኔታዎች ቅድሚያ የሰጠሃቸው ነገሮች ጠቋሚ ናቸው:: በሌላ አባባል ሁል ጊዜ ስታደርግ ራስህን

Scanned with CamScanner

የምታገኘው ነገር የሕይወትህን ቅደም ተከተል ያሳያል፡፡ አእምሮህ የሚያስበው ሃሳብ፣ እግርህ የሚራመድበት አቅጣጫና እጆችህም ለማድረግ የሚቀናቸው ጉዳዮች የሕይወትህን ቅኝት አመልካቾች ናቸው፡፡ ይህ ቅኝት ከአላማህ አንጻር መቃኘቱን እርግጠኛ ሁን፡፡ አለዚያ ሙዚቃው የማይጫወተውን ቅኔ ስትቀኝ በመኖር ራስህንም ሆነ ሌላውን ግራ ታጋባለህ፡፡

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው በአላማ ለመኖር የሚጠቅሙ ምክሮች፡-

1. አእምሮህን ተጠቀም
2. በየቀኑ ገጠመኝህና በስሜትህ አትነዳ
3. ተግባሮችህን ከዓላማህ አንጻር ቃኛቸው

የእለቱ ተግዳሮት የሚያመጣብን ትግልና የጊዜው መልካም ገጠመኝ የሚሰጠን ጊዜአዊ ደስታ ልንገነባው ከሚገባን አጠቃላይ የሕይወት ዓላማ አይነ-ህሊናችንን ይጋርዱታል፡፡

3

ጫማ የሚያደርግ የለም

አጋጣሚን የመጠቀም ቁልፍ

አንድ አይነት “እድል” ያጋጠማቸው ሁለት ሰዎች እንዴት የተለያየ የስኬት ደረጃ ይኖራቸዋል? ሁለት ሰዎች በአንድ ቤት ተወልደው፣ በተመሳሳይ ቤተሰብ እጅ አድገው፣ በአንድ ከተማ ኖረው፣ በአንድ አይነት ትምህርት ቤት ተምረው እንዴት የተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛሉ? እነዚህ ሰዎች ተመሳሳይ እድል አግኝተው አንዱ በስኬት ሲዘልቅ ሌላው በተራ ነገር ተወስኖ ሲቀር ጥያቄ የሚፈጥር ጉዳይ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በእጃው የገባውን እድል አያዩትም፣ ስለዚህ በፍጹም አይጠቀሙበትም፡፡ ለአንድ ነገር መታደል አንድ ነገር ነው፣ ያንን እድል መጠቀም መቻል ደግሞ ሌላ ነገር፡፡ አንዳንድ ሰዎች በፊታቸው ያለውን እድል ለማየት አይናቸውን ያለመከፈታቸው እውነታ የስኬታማዎችን ካምፕ ከስኬተ ቢሶቹ የሚለየውን መስመር ያሰምረዋል፡፡

ከብዙ አመታት በፊት በዘመኑ ሰለጠነ ከሚባል ከአንድ የአውሮፓ አገር ሁለት ሰዎች ወደ አንዲት በስልጣኔ ወዳልገፉች ደኃ አገር የጫማ ፋብሪካን ለመክፈት እንደተላኩ ይነገራል፡፡ በዚያች ደኃ አገር ውስጥ አንድም ጫማ የሚያደርግ ሰው የለም፣ ሁሉም ባዶ እግሩን ነው የሚሄደው፡፡ አንደኛው ሰው በሶስት ሳምንት ወደመጣበት ካምፓኒ እንዲህ የሚል መልእክት ላከ፣ “ማንም ሰው ጫማ የማያደርግበት ሃገር ልካችሁኝ

እንዴት ጫማ ሽጥ ትሉኛላችሁ?" ሁለተኛውም በዚያው ሰሞን እንዲህ የሚል መልእክት ለአለቆቹ ላከ፣ "ማንም ጫማ የሚያደርግ ሰው የለም። ስለሆነም ታላቅ የጫማ ገበያ እድል ያለበት ስፍራ ነውና እዚያ ያለውን ጫማ በሙሉ ላኩ፣ ፋብሪካውም በአስቸኳይ ይከፈት"። ሁለት ሰዎች፣ አንድ አይነት ሁኔታ፣ የተለያየ እይታ! አንዱ ጫማ የማያደርጉ ሰዎች መካከል እንዴት ጫማ ይሸጣል ብሎ ሲያስብ፣ ሌላኛው ጫማ ያለማድረጋቸውን ሁኔታ ጫማ የመሸጫ እድል አድርጎ ወሰደው።

"ጨለምተኛው በፊቱ ባገኘው እድል ሁሉ ውስጥ ያለውን አስቸጋሪ ነገር ያያል፣ አዎንታዊው በገጠመው ችግር ሁሉ ውስጥ ያለውን እድል ይመለከታል" - Winston Churchhill

ቆም በል! ዙሪያህን ተመልከት! ዙሪያህን ብዙ አስገራሚ እድሎች ሞልተውታል። ልታውቃቸው የምትችላቸው ሰዎች፣ ልትሰራቸው የምትችላቸው ስራዎች፣ ልትማራቸው የምትችላቸው የትምህርት አይነቶች ... እድሉ ብዙ ነው።

በዙሪያህ ያለውን እድል ለማየት ማንነትህን ብትከፍተው ለማዘን፣ ለማቀርቀርም ሆነ ተስፋ ለመቁረጥ ጊዜ እንደማይኖርህ ወዲያው ይገለጥልሃል። ምናልባት የሌለህንና በዙሪያ የከበበውን አጉል ነገር ብቻ እያየህ ስጋት ውስጥ ትኖር ይሆናል። ይህንን ግን አስብ - በዙሪያህ ያለው ጨለማ ከሆነ፣ አስገራሚ የሆነ ብርሃንን የማብራት እድል እንደሆነ አትዘንጋ። የሚያደርገውን በማያውቅ ሰው የተሞላ አካባቢ ካለህ እነዚህን ሰዎች የማሰልጠን ታላቅ እድል እንዳለህ አስታውስ። ራስህን ጸብ ባለበት ቦታ ካገኘኸው የሰላም አምባሳደር የመሆን ታላቅ እድል እንዳጋጠመህ መቁጠር ትችላለህ። ይህ እንዲሆን ግን የተዘጋጀ ማንነት ያስፈልግሃል።

በዙሪያ ያለውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም እንድትችል የሚከተሉት እውነቶች ያግዙሃል ብዬ አምናለሁ።

ጨለምተኝነትን አስወግድ

ጨለምተኛ (Pessismist) የሆነ ሰው አሉታዊ ሰው ነው። አሉታዊ ማለት የአዎንታዊ ተቃራኒ አመለካከት ነው። አዎንታዊ ሰው በይሆናልና በይቻላል የተሞላ ሰው ነው። በእያንዳንዱ ገጠመኝ ውስጥ ጥሩውን ጎን ለማየት ቀና ይላል። ጨለምተኛው ግን ዘወትር ጨለማውን፣ ከስረቱንና ውድቀቱን ለመቁጠር የተዘጋጀ ማንነት አለው። እንዲህ አይነት ሰው ሳይወድቅ የወደቀ ሰው ነው። ጨለምተኛ ሰው በራሱ ላይ ክፉን "የሚተነብይና" የራሱን "ትንቢት"ራሱ የሚያስፈጽም አሳዛኝ ሰው ነው። "እወድቃለሁ፣ አይቻልም፣ መሰናከሉ ብዙ ነው ..." ብሎ ስለሚያስብ እነዚህን ነገሮች ለማስተናገድ የተዘጋጀ ማንነት አለው። የሚያየውም ያንን ነው፣ የሚሄደውም ወደዚያው ነው፣ የሚወድቀውም እዚያው ላይ ነው! ይህ ሰው ስኬተ-ቢስ ሆኖ ከመቅረት በቀር ሌላ ምንም አማራጭ የለውም። አዎንታዊ ሰው የዚህ ተቃራኒ ነው። ከማይቻል ውስጥ የሚቻልን ነገር፣ ከመውደቅ ውስጥ የመነሳትንና የመዝለቅን እድል፣ በጨለማ ውስጥ የብርሃን ምንጭ የመሆንን ገጠመኝ የሚያይ ማንነት አለው።

"ጨለምተኛ ሰው ማለት ከሁለት ክፉ ነገሮች መካከል አንዱን የመምርጥ ሁኔታ ሲያጋጥመው ሁለቱንም የሚመርጥ ሰው ነው" - Oscar Wilde

የገጠመህን ሁኔታ ሁሉ በምን እይታ እንደምታየው የመምረጥ ሙሉ መብት አለህ። ጨለምተኝነትን ከመረጥክ እይታህን ሁሉ የማደብዘዝ ተጽእኖ ያስከትልብሃል። ምርጫህ ሁሉ ጤና ቢስ ይሆናል። አዎንታዊነትን ስትሞላ ግን ከክፉ ነገር ውስጥ እንኳ ሳይቀር መልካም ነገርን ጨምቆ ለማውጣት የሚያስችልን ብሩህ እይታ ታገኛለህ።

Scanned with CamScanner

ሁኔታዎችን ወደ መኖር አምጣቸው

በስኬታማና በስኬተ-ቢስ ሰው መካከል ካሉት ዋነኛ ልዩነቶች መካከል ይህ እውነታ አንዱ ነው:: ስኬታማ ሰዎች ቁጭ ብለው ሁኔታዎች ወደመሆን እስኪመጡ አይጠብቁም፣ ሁኔታዎችን በመነካካት ወደመሆን ያመጧቸዋል እንጂ:: ይጀምራሉ፣ ይንቀሳቀሳሉ፣ ያነጋግራሉ፣ ያንኳኳሉ ... :: ስኬተ-ቢስ ሰዎች ሁኔታዎች ወደመኖር እስኪመጡ ቁጭ ብለው ይጠብቃሉ:: ከመጡ ጉድለታቸውን ሲቆጥሩ ካልመጡ ደግሞ ባለመምጣታቸው ሲነጫነጩ ይታያሉ:: ይህ ደግሞ በራስ ላይ መከራን እንደመደራረብ ነው:: ምናልባት ያደከበት አካባቢ ካልደገፉት፣ ካልጎተቱት፣ ካላደረጉለትና ካልተቆጣጠሩት የማይንቀሳቀስ ህዝብ የሞላበት አካባቢ ቢሆንም እንኳ፣ አንተ ግን ከዚያ ለየት ለማለት መወሰን ትችላለህ:: የሚያስብ አእምሮ፣ የሚጀምሩ እጆችና የሚራመዱ እግሮችን ማዳበር ትችላለህ:: ይህ የሚሆነው ግን አሁን ካለህበት ሁኔታ የተሻለ ነገር ውስጥ ለመግባት በመቁረጥና ነገሮችን ወደ መኖር ለማምጣት በመንቀሳቀስ ነው::

"አንዳንድ ሰዎች ነገሮችን ወደመኖር ያመጣሉ፣ ሌሎች ነገሮች ወደመኖር ሲመጡ ዝም ብለው ያያሉ፣ ሌሎች ደግሞ በሚከናወነው ነገር ከመደነቅ ያለፈ ነገር የላቸውም" – Unknown Source

ከየትኛው ወገን ነህ? ሰዎች ባላቸው ብቃት ተጠቅመው ከስኬት ወደ ስኬት ሲዘልቁ የእነሱን ነገር እንደ ድራማ ከሚያዩት ነህ? ሰዎች ከአንዱ ከንዋኔ ወደሌላኛው ሲሻገሩና ጊዜአቸውን ለመልካም ስኬት ሲያውሉት ከሚያደንቁትና ከሚያወሩት ነህ? ወይስ ጨዋታው መካከል ነህ? አሁን ላነሳሳህ፣ ጨዋታው መካከል ግባ! በመጀመሪያ ራስህን አነሳሳ፤ በመቀጠልም ነገሮችን ቀስቅስ:: የሌለው ነገር በአንተ ምክንያት ወደመኖር ይምጣ:: ያለው ነገር በአንተ ምክንያት ወደ ተሻለ ደረጃ ይደግ::

እጥረትን ወደ ገቢ ምንጭ ቀይር

በዚህ አለም ላይ ገንዘብ የሚከፈልህ ከፋዮችህን ለተጋፋቸው ችግር ለምትሰጠው መፍትሄ እንደሆነ አትዘንጋ:: ችግር ባለበት ስፍራ መፍትሄ ሰጪዎች ይፈለጋሉ:: ሃኪሞች የህመምን ችግር ይፈታሉ፣ መካኒኮች የመኪናን ችግር ይፈታሉ፣ አካውንታንቶች የገንዘብ አያያዝን ችግር ይፈታሉ:: ይህንንም በማድረግ ገንዘብ ያገኛሉ:: በብዙ ስፍራዎች ግን ችግር አራጋቢዎች እንጂ መፍትሄ አቅራቢዎች ላታገኝ ትችላህ - እንዴት ያለ ታላቅ እድል! የመፍትሄ ምንጭ ለመሆን ራስህን ማዘጋጀት ትችላለህ:: በዙሪያህ ችግር ያለበትን ሁኔታ ስትመለከት፣ ስለችግሩ ከማውራትና ጥፋተኛውንና የሚወቀሰውን ሰው ከመፈላለግ ይልቅ፣ ያንን ችግር የመቅረፊያውን ብልሃት ተማርና ተመለስ፣ የመፍትሄ ሰው ትሆናለህ - ስኬትህ ያለው እዚያ ጋር ነው! እምቢታን የመጨረሻ መልስ አድርገህ አትቀበል:: እምቢ ያለህ ነገር እሺ እስኪልህና መፍትሄ እስኪገኝለት ድረስ መንገድን ፍጠር:: መውደቅንና ተስፋ መቁረጥን የመጨረሻ መልስ ላለማድረግ ቁረጥ:: ይልቁንም ሁኔታዎቹን ወደ እድል ለውጣቸው::

"ችግራችን የችግር መኖር አይደለም:: ችግራችን፣ ችግር በፍጹም መከሰት የለበትም ብለን አስበን ችግር መኖሩን እንደችግር መቁጠራችን ነው" – Theodore Rubin

ችግር የሌለበት ስፍራና ሕይወት የትኛው ነው? ሕጻን መጫወቻ የመቀማት ችግር አለበት:: ወጣቱ በጓደኛ የመገፋት ችግር አለበት:: ያገባው ያለመግባባት ችግር አለበት:: የወለዱት የልጆች አስቸጋሪነት ይጋፋቸዋል:: ልጆቹን አሳድጎ ከቤቱ ካሰናበተ የከረመው ደግሞ የእድሜ ጫና የሚያስከትለው ችግር አለበት:: በዚህ ምድር ላይ ስትኖር ይህቺ ዓለም ከአንዱ ችግር ወደ ሌላኛው ችግር እየተቀባበለች ታኖርሃለች:: አመለካከትህን ብትቀይር ግን ችግርን ወደ እድልና ወደ ስኬት መሰላልነት መቀየር ትችላለህ:: አሁን ማንበብህን አቁምና በዙሪያህ ሰዎች የሚቸገሩበትን ነገር እስቲ አስብ:: አንድ ነገርን ማግኘትህ አይቀርም::

Scanned with CamScanner

ይህ ችግር እስካሁን ያለውና ሊለወጥ ያልቻለው መፍትሄ የሚሰጠው ሰው ስላልተገኘ ነው:: መፍትሄ ሰጪ የማይገኝበት ምክንያት ደግሞ ችሎታው ያለው ሰው ሲጠፋ ወይም ደግሞ ችሎታው እያለው ፈቃደኝነቱ ያለው ሰው ሲታጣ ነው:: ሁኔታው ግን ምን አይነት እድል ሊሰጥህ እንደሚችል አስበው:: መፍትሄ ፍጠርለትና አንድ ነገር አድርግ::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው አጋጣሚን የመጠቀም እርምጃዎች:-

1. ጨለምተኝነትን አስወግድ
2. ሁኔታዎችን ወደ መኖር አምጣቸው
3. እጥረትን ወደ ገቢ ምንጭ ቀይር

ራስህን ጸብ ባለበት ቦታ ካገኘኸው የሰላም አምባሳደር የመሆን ታላቅ ሊድል እንዳጋጠመህ መቁጠር ትችላለህ::

4

ጨምዳዳው መቶ ብር

ማንነትን የመቀበል ቁልፍ

የማንነትህን ዋጋ የሚወስነው ምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች የማንነታቸውን ዋጋ የሚመዝኑት ካሳለፉት መከራና ከደረሰባቸው ችግር አንጻር ነው:: የደረሰባቸውን የኑሮ ውጣ ውረድ በአካላቸውና በኑሮአቸውም ላይ ያደረሰውን ጉዳት በቀጥታ ከማንነታቸው ዋጋ ጋር ያዛምዱታል:: ሲቸገሩና ሲጎሳቆሉ የማንነታቸውን ዋጋ ይቀንሱታል:: በአንጻሩ ነገሮች በመልካም ሲሄድላቸውና የተሳካላቸው ሲመስላቸው ለራሳቸው የሚሰጡትን ዋጋ ከፍ ያደርጉታል:: ሰዎችም ካለማቋረጥ ይህንኑ መልእክት ለህሊናው እንዲናገሩ ይፈቅዱላቸዋል:: ውጤቱም የወደቀ ማንነትን ነው::

በአንድ በዝቅተኝነት ስሜት የተሙቱ ሰዎች ለምክር በሚመጡበት ማእከል ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል:: ችግራቸው አንድ ነው፣ የኑሮአቸው ሁኔታ በራሳቸው ላይ ያላቸውን አመለካከት ደብድቦ ጥሎታል:: በራሳቸው ላይ የወደቀ አመለካከት አላቸው:: ይህ ሰው በምን መልኩ ከዚህ አመለካከት ሊያወጣቸው እንደሚችል ካሰበ በኋላ አንድን ምሳሌ ነገራቸው:: በእጁ አንድ ድፍን መቶ ብር ይዟል:: ወደ ሰዎቹ ዘወር አለና፣ "የዚህ ብር ዋጋ ስንት ነው?" አላቸው:: የሁሉም መልስ እንደተጠበቀው፣ "መቶ ብር" የሚል ነበር:: የሚቀጥለው ጥያቄ፣ "ይህ ብር ምን ሊገዛ ይቻላል" የሚል ነበር:: ሁሉም

በመሸቀዳደም ምን ሊገዛ እንደሚችል መናገር ጀመሩ:: በመቀጠልም፣ ይህንን መቶ ብር በመዳፉ አጅግ ጨመደደው፣ ከዚያም ወደ መሬት ጣለውና ረገጠው:: በእጁ አንስቶ ከጨመደደው በኋላ ያንኑ ጥያቄ ጠየቃቸው፣ "የዚህ ብር ዋጋ ስንት ነው?":: የሁሉም መልስ እንደቀድሞው፣ "መቶ ብር" የሚል ነበር:: ሁለተኛውንም ጥያቄ ደገመው፣ "ይህ ብር ምን ሊገዛ ይቻላል?" የሚል ነበር:: መልሳቸው እንደቀድሞው ነበር:: ከዚያም መልእክቱን አስተላለፈላቸው - "ይህ ብር ተጨማደደ፣ ወደቀ፣ ተረገጠ፣ ... ዋጋው ግን ያው ነው:: የእናንተም ዋጋ እንዲሁ ነው:: ምንም አይነት ነገር በሕይወታችሁ ቢያልፍ፣ ዋጋችሁ ግን ያው ነው - የውጪ ገጠመኞቻችሁና ሁኔታችሁ የማንነታችሁን ዋጋ መቀነስም ሆነ መጨመር አይችልም"::

"አንተነትህን የያዘው የሆንከው ማንነትህ አይደለም፣ ነኝ ብለህ ያሰብከው ሃሳብህ እንጂ" - Unknown Source

ከተወለድክባት ቀን ጀምሮ ያለፍክባቸውን ሁኔታዎች መለስ ብለህ ተመልከታቸው:: የወደቅክባቸውንና የተነሳህባቸውን፣ ያዘንክባቸውንና የተደሰትክባቸውን፣ የብቸኝነትህን ጊዜና በወዳጆች የተከበብክባቸውን ጊዜአት ... አስባቸው:: እነዚህ ሁኔታዎች የተለያዩ የስሜት ከፍታዎችንና ዝቅታዎችን እንድታሳልፍ ዳርገውሃል፣ ሆኖም በማንነትህ ላይ ጥቂት እንኳ የዋጋ መቀነስ ተጽእኖ የላቸውም:: ማንነትህ፣ በምንም ሁኔታ ውስጥ ብታልፍም ያው ማንነትህ ነው:: ስኬታማ ሆንክም አልሆንክ፣ ባለጠጋ ሆንክም አልሆንክ፣ እነዚህ ነገሮች ከማንነትህ ጋር በፍጹም አይገናኙም:: በማንነትህ ላይ ያለህ አመለካከትና ለማንነትህ የሰጠኸው ዋጋ ግን በስኬታማነትህ ላይ ታላቅ ተጽእኖ ሊያመጣ ይችላል:: ያለፈው ታሪክህ፣ አሁን የምታልፍበት የኑሮ ጫናም ሆነ ያለህና የሌለህ ነገር በአንተነትህ ዋጋ ላይ ተመን እንዲያስቀምጡበት የምታደርገው አንተው ብቻ ነህ:: ሰው የመሆንህ ክቡርነት በፍጹም በዋጋ ሊተመን ስለማይችል፣ ከፍም ሆነ ዝቅ ማለት አይችልም:: በራስህ ላይ ያለህ ግምት ግን ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል:: ይህ ሁኔታ

ደግሞ አመልካችነቱ የስሜትን ከፍታና ዝቅታ እንጂ የማንነትን ዋጋ ከፍታና ዝቅታ አይደለም::

ዋጋህን ሳትቀናንስ፣ ካለፈውና ከአሁኑ ሁኔታህ ላይ አይኖችህን አንስተህ በፊትህ ወዳለው መልካም የወደፊት ስኬት እንድትዘልቅ የሚከተሉትን እውነታዎች ማሰላሰሉ ጠቃሚ ነው::

ሰዎች የሚሰጡህን ቅጽል ስም አትቀበል

አንዳንድ ሰዎች ከፈቀድክላቸው በአንተ ላይ ተረማምደው የመሄድ ባህሪይ አላቸው:: ከራሳቸው ጥቅም አንጻር የሚቀርቡህ፣ የአንተ መውደቅ ለእነሱ መነሳት የሚጠቅም የሚመስላቸውና ለመብሰል ብዙ የሚቀራቸው ሰዎች በአካባቢህ አይጠፉም:: ለእነዚህ ሰዎች ልቦናህን ከከፈትክና በአንተ ላይ፣ ስለአንተና ለአንተ የሚያወሩት ነገር ተጽእኖ እንዲያመጣብህ ከፈቀድክለት መውጫና መግቢያ ያሳጡሃል:: በምትኩ፣ አንተ ያልፈቀድክለት ስም በአንተ ላይ ምንም ተጽእኖ እንደማይኖረው በማመን ሰዎች ያሰመሩብህን መስመር አልፈህ ለመሄድ መነሳት አለብህ:: ሰዎች የሚያውቁትን ነው የሚያደርጉት:: በሌላ አባባል፣ ከዚህ የተሻለ ቢያውቁ ኖሮ በዚህ ሁኔታ አያስተናግዱህም ነበር:: የሰጡህ ስም ሳይሆን ለዚያ ሁኔታ የሰጠኸው ምላሽ በወደፊትህ ላይ ወሳኝ ነው::

"ቅጽል ስሞች በሰው ላይ የመጣበቅ ባህሪይ አላቸው፤ በተለይም ከፉ ቅጽል ስሞች እንደማይለቁ ማስቲሾች ናቸው" – Thomas Chandler

የቅጽል ስም ጥቃት የደረሰበት አንድ ሰው፣ "ቅጽል ስም ሰይጣን በአንድ ሰው ላይ ከሚወረውራቸው ጠንካራ ድንጋዮች መካከል የከፋው ድንጋይ ነው" ብሎ ተናገረ፣ እውነቱን ነው:: ለሰዎች ቅጽል ስም የመስጠት ባህል በአለም ላይ ሁሉም አገር የሚጋራው ባህል ነው:: የልጅነታችንን ዘመን ዘወር ብለን ስናስታውሰው በአካባቢያችን

Scanned with CamScanner

ከእውነተኛው ስማቸው የተለየ ስም የተሰጣቸው ልጆች በርካታ ናቸው:: የሚያስገርመው ግን አብዛኛዎቹ ቅጽል ስሞች ጥሩ ስሜት የሚሰጡ ሳይሆኑ ሰውን የሚያንቋሽሹ ናቸው:: ሰዎች የሚሰጡህ ስም ሊጎዳህ የሚችለው ልቦናህን ስትሰጠውና የመጎዳት ዝንባሌ ሲኖርህ ብቻ ነው:: አሉታዊ ቅጽል ስምን በሰዎች ላይ መለጠፍ የሚወዱ ሰዎች ብርታትን የሚያገኙት ሰዎቹ በተሰጣቸው ቅጽል ስም ግራ ሲጋቡ ሲያዩ ብቻ ነው::

የሆነልህን እንጂ የሆነብህን አትቁጠር

ሳታሸንፍ በፍጹም እዚህ አልደረስክም:: አንተ የአሸናፊዎች ምሳሌ እንጂ በፍጹም የተሸናፊዎች ምልክት አይደለህም:: የአየሩን መለዋወጥ፣ የኢኮኖሚውን ከፍና ዝቅ ማለት፣ ከሰዎች የሚሰነዘርብህን ደስ የማያሰኙ ሁኔታዎች ... አልፈህ እዚህ ደርሰሃል:: ከአሁን ወዲያ ደግሞ ከተሳሳትካቸው ነገሮች ትምህርትን፣ ከተሳኩልህ ጉዳዮች ደግሞ ድፍረትን በመያዝ ወደፊት የመሄድ ሃላፊነት አለብህ:: ማታ እቤት ስትገባ በሰላም መግባትህን አስብ እንጂ ከኪስህ የጠፋውን ገንዘብ ወይም የሞባይል ቀፎ በማሰብ፣ ወይም በመንገድ ላይ ያበሳጨህን ሰው በማሰላሰል አእምሮህን አትሙላው:: ውስጥህን በይሆናልና በይቻላል መሙላት ከአንተ በፊት ያለፉ ሰዎችን አስደናቂ ፈለግ የመከተል አስገራሚ እርምጃ እንጂ የቅዠት ምልክት አይደለም:: የሆነልህን መልካም ነገር አእምሮህ ውስጥ ስፍራን ስጠውና በመኮትኮት አሳድገው:: በተቃራኒው ደግሞ ጤና ቢሱን ሃሳብ ስፍራ በመንፈግ አስርበውና እንዲሞት አድርገው::

"ከሃዘኖችህ ይልቅ ሃሴቶችህን፣ ከጠላቶችህ ይልቅ ደግሞ ወዳጆችህን ቁጠር" - Irish Proverb

ስለሚወዱህ ሰዎች ከማሰላሰልና ስለሚጠሉህ ሰዎች ከማሰብ የትኛው ጥሩ ስሜት ይሰጥሃል? የሚወዱህ ሰዎች የነገሩህን የፍቅርና የአክብሮት ቃል ከማሰብና የሚጠሉህ

ሰዎች የነገሩህን ስሜትን የሚወጋ ቃል ከማሰላሰል የቱ ይሻልሃል? ምርጫው የአንተ ነው:: ቁጭ ብለህ የማይቀበሉህ ሰዎች ማን ማን እንደሆኑ ከመቁጠር፣ የሚወዱህንና የሚቀበሉህን ሰዎች መቁጠር በስኬትህ ላይ ታላቅ ተጽእኖ አለው:: ጨለማን በብርሃን አሸንፍ እንጂ በጨለማ አትሸነፍ::

ራስህን አክብር

ራስህን ካላከበርክ ማንም ሰው እንደማያከብርህ እወቅ:: ራስህን ማክበርህን ለማወቅ ስለ ራስህም ሆነ ስለ ሃገርህ ሰዎች፣ ስለ ወገኖችህ የምትናገረውን ንግግር አጢነው:: ራስህን ሳታከብር ወገንህን ልታከብር አትችልም:: ወገኑን የናቀ ሰው በቅድሚያ የናቀው ራሱን ነው:: በሌላ ጎኑ፣ አለባበስህ፣ ለራስህ የምትሰጠው ትኩረት፣ የምትገኝባቸው ስፍራዎች፣ የምትመርጣቸው የጓደኛ አይነቶች ለራስህ የሰጠኸው ዋጋ ምልክቶች ናቸው:: ንጹህ ነኝ ብለህ እያሰብክ ቆሻሻ ቦታ ራስህን ልታገኘው አትችልም:: ጨዋ ነኝ ብለህ እያሰብክ ራሳቸውን ከተራ ነገር ለማውጣት ከማይፈልጉ ሰዎች ጋር ማሳለፍ አትችልም:: የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ለራስህ የሰጠኸው ዋጋ ነጸብራቆች ናቸው::

"ለራሳችን ያለንን ክብር አሳልፈን ካልሰጠናቸው በስተቀር ሰዎች ሊወስዱብን አይችሉም" - Mahatma Gandhi

ይህንን አትዘንጋ:- ሰዎች ከሰጠሃቸው ሙብት የበለጠ ምንም አይነት ሙብት በአንተ ላይ ሊኖራቸው አይችልም:: እንዳይንቁህ ማድረግ አትችልም፣ ራስህን በማክበር ግን ንቀታቸውን ቦታ ልታሳጣው ትችላለህ:: ስለአንተ ክፉ እንዳያወሩ ማድረግ አትችልም፣ ያወሩትን ክፉ ነገር ተቃራኒ በመኖር ግን ወሬአቸው ውሸት እንደሆነ የማሳየትን ሙብትህን ግን ሊወስዱብህ አይችሉም:: አብረሃቸው ለማሳለፍና በማንነትህ ላይ ተጽእኖ እንዲያመጡ የፈቀድክላቸው ሰዎች ብቻ በማንነትህ ላይ ያለህን አመለካከት ይወስናሉ፣ ይህንን ደግሞ መቆጣጠር ትችላለህ::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ማንነታችንን እንድንቀበል የሚረዱን አስፈላጊ ቁልፎች:-

1. ሰዎች የሚሰጡህን ቅጽል ስም አትቀበል
2. የሆነልህን እንጂ የሆነብህን አትቁጠር
3. ራስህን አክብር

ሰው የመሆንህ ክቡርነት በፍጹም በዋጋ ሊተመን ስለማይችል፣ ከፍም ሆነ ዝቅ ማለት አይችልም::

5

መራራው ሂትለር

ካለፈው ታሪክ የመፋታት ቁልፍ

የልጅነት አስተዳደጋችን በወደፊት ማንነታችን ላይ ምን ያህል ተጽእኖ አለው? የልጅነትንና የሊጋነትን ዘመን ፍጹም ፍቅር በተሞላበት ቤት ለማደግ የበቃ ልጅ የታደለ ነው:: ብዙዎች ግን ይህንን እድል አያገኙትም:: አንዳንዶች ርህራሄ በሌላቸው ቤሰቦች እጅ ሲያድጉ፣ ሌሎች ደግሞ ከቤተሰባቸው ጋር እንኳን የማደግ እድል አያገኙም:: የመደብደቡ፣ የአስገድዶ መደፈሩ፣ በማያፈናፍን ችግር ውስጥ ማለፉ … ብዙዎች ወደ አቅመ-አዳም (አቅመ-ሄዋን) ሲደርሱ በውስጣቸው ተሸከመው የሚመጡት አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል አይደለም:: የቀናውና የሚያደርገውን ያወቀው ብቻ ከዚያ ተጽእኖ ይላቀቃል::

የአዶልፍ ሂትለር ታላቅ ወንድም የአባቱ ጨካኝነትን ለማምለጥ በ13 አመቱ ነበር ከቤቱ በርሮ የጠፋው:: ይህ ልጅ ከቤቱ ከሄደ በኋላ የሂትለር አባት ክፋቱን በሰባት አመቱ ለጋ ልጅ በሂትለር ላይ በእጥፍ ጨመረው:: ሂትለር በአባቱ እጅ አሰቃቂ አመታትን አልፏል:: ምርጫውን ተከልክሎአል:: አርቲስት ለመሆን ይመኝ የነበረው ሂትለር በአባቱ አስገዳጅነት የሲቪል ሰራተኛነት አቅጣጫን እንዲከተል ተገደደ:: የሂትለር ትምህርት ውጤቱ አጥጋቢ ስላልነበር የአባቱን የቁጣ እጅግ አባባሰው:: የአይሁድ ዘር

Scanned with CamScanner

እንዳለበት የሚነገረው የሂትለር አባት ከፋት በሂትለር ልብ ውስጥ አይሁድን የመጥላት ዘርም እንደዘራበት ይነገራል:: አባቱ ከሞተ በኋላ፣ ሂትለር በ13 አመቱ የቤት ሃላፊትን በጫንቃው ላይ ተሸከመ:: በእናቱ ሞት ምክንያት በኋላ በጉዲፈቻ ያድግ የነበረው ሂትለር ያንን ገቢ በመከልከሉ የጎዳናን ሕይወት ቀምሷል:: በብዙዎች እንደሚታመነው፣ ሂትለር በልጅነቱ ያሳለፈው ስቃይ ውስጡ ከጨመረበት መራራነት እንዳልተላቀቀና በሕይወቱ ያደረጋቸው አሰቃቂ ተግባሮች የዚያ ልምምድ ተጽእኖ እንደሆኑ ይታመናል:: ሂትለር ቢያንስ ለ46 ሚልዮን ሰዎች መሞትና ለብዙ ንብረት መውደም ምክንያት የሆነ ሰው ነው::

"ጥላቻና መራራነት ማለት አንዲትን አይጥ ለመግደል ቤትህን በእሳት ማቃጠል ማለት ነው" - Henry Fosdick

አንዳንድ የስነ-ልቦና ጥናቶች፣ አንድ ልጅ በአምስት አመቱ የወደፊቱን የሚወስነውን ብዙውን ማንነቱን ገንብቶ እንደሚጨርስ ይጠቁሙናል::

አዋቂዎች ሁሉ የሚስማሙበት እውነታ፣ አንድ ልጅ በመጀመሪያዎቹ አምስትና አስር አመታት የሚያሳልፋቸው ሁኔታዎች በወደፊት ማንነቱ ላይ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው:: አንድ ሰው በእድሜ እያደገ ሲሄድ በለጋነቱ የደረሰበትን አስከፊ ሁኔታ ወደ ኋላ ለመጣልና ከመራራነት ለመውጣት አስፈላጊውን እርምጃ ካልወሰደ የወደፊት ማንነቱ መራራና ለሕብረተሰብ ጠንቅ የሚሆኑ ባህሪያትን የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል::

አንዳንድ ሰዎች የልጅነታቸውን አሉታዊና ጤና ቢስ ልምምድ በስሜታቸው ላይ ካመጣው ተጽእኖ ሳይላቀቁ ወደ ትዳር አለም ውስጥ ይገባሉ:: ቁጣን፣ ጸበኝነትን፣ ጠርጣራነትንና የመሳሰሉትን ለትዳር ጠንቅ የሆኑ መራራ ነገሮች ይዘው ስለሚገቡ ብዙም ሳይቆዩ ለመለያየት ምክንያት ይሆናሉ:: ሌሎች መራራነትን፣ ጥላቻንና በአስተዳደግ ዘመናቸው የተጎነጩትን የውስጥ ቂም ይዘው ወደ አመራር ይዘልቃሉ - እንዴት አይነት ስህተት! ካለፈው ሕይወት ተጽእኖ በስኬታማ ሁኔታ ራሱን መርቶ

ያላወጣ ሰው ሌላውን ለመምራት ሲሞክር ሊያስከትለው የሚችለው ጉዳት ቀላል አይደለም:: ወደፊት ለመዝለቅና ስኬታማ ሕይወት ውስጥ ለመግባት ካለፈው መፋታት የግድ ነው:: ይህንን ለማድረግ የሚጠቅሙ ሃሳቦች እነሆ:-

ሙሉ ሃላፊነትን ውሰድ

በሕይወትህ የተከሰቱትን አስከፊ ሁኔታዎች ለመቆጣጠር እድሉ ያልነበረህ ሰው ብትሆንም እንኳ፣ አሁን ግን ለሆነብህ ነገር የምትሰጠውን ምላሽ የመወሰን እድሉ አለህ:: ስለሆነው ነገር ሰውን እየወቀሱ መኖር ሁኔታውን ያብሰዋል እንጂ ምንም አይጠቅምህም:: አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸው ስላለበት ሁኔታ የማይወቅሱት ሰው የለም - ቤተሰብን፣ ፍቅረኛን፣ የትዳር ጓደኛን፣ መንግስትን፣ የኃይማኖት መሪዎችን _ ተወቃሹ ብዙ ነው:: እውነታው ግን ይህ ነው:- በሕይወትህ ለሆነው፣ በመሆን ላይ ላለውና ወደፊትም ለሚሆነው ነገር ሙሉ ሃላፊው አንተ ነህ:: የሆነውንና የሚሆነውን መቆጣጠር ባትችልም እንኳ፣ ለተከሰተው ሁኔታ የምትሰጠውን ምላሽ መወሰን ትችላለህ:: በአለም ላይ የሚያስገርም ስኬት ውስጥ የገቡ ሰዎች አብዛኛዎቹ በልጅነታቸውም ሆነ ከጎለመሱ በኋላ በሰዎች እጅ አሰቃቂን ነገር ያሳለፉ ሰዎች ናቸው:: እነዚህን ሰዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ስለግል ሕይወታቸው ሙሉ ሃላፊነትን የመውሰዳቸው ጉዳይ ነው::

"ስለ ህይወትህ በግልህ ሃላፊነትን መውሰድ አለብህ:: በዙሪያህ የሚከናወነውን ነገር፣ የአየሩን ጸባይና ነፋሱን መቆጣጠርና መለወጥ አትችልም፣ ራስህን ግን መለወጥ ትችላለህ" – Jim Rohn

ከሆነብህም ሆነ ከሆነልህ ነገር ውስጥ የምታተርፈው ዋነኛ ቁም ነገር የማንነት መለወጥ ነው - ለመልካም የሆነ መለወጥ ማለቴ ነው:: ይህ ደግሞ የውሳኔ ጉዳይ ነው:: ልትለውጣቸውና ልትቆጣጠራቸው ከማትችላቸው ነገሮች ጋር መታገሉን ተውት

Scanned with CamScanner

በማድረግ መለወጥ የምትችለውን ማንነትህን ወደመለወጥ ዘወር ማለት አለብህ:: አንዱ ምርጫህ፣ ትናንት የሆነብህን በማሰብ መቆጣት፣ መበሳጨትና መራራ ምላሾችን ለመስጠት መዘጋጀት ነው - ይህኛው ይቅርብህ:: ሌላኛው ምርጫህ ግን፣ "የሆነው ሆኗል፣ አሁን ወደፊት በማየት የሕይወቴን ሁኔታ በቁጥጥር ስር አውላለሁ" የሚል ነው - አስገራሚ ምርጫ!

ሰዎችን ይቅር በል

በዚህ ምድር ላይ ስትኖር ሰዎች ሳይነኩህ መኖር በፍጹም አትችልም:: አንዳንድ ሰዎች ሆን ብለውና አስበውበት ሊጎዱህ ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ በፍጹም ባላሰቡበት ሁኔታ አንተን የሚጎዳ ሁኔታ ውስጥ ጨምረውህ ሊሆን ይችላል:: እንደውም ሁኔታውን ቀረብ ብለህ ካሰብከው፣ ብዙዎቻችን የምንጎዳው በቅርብ ሰው ነው:: ልባችንን የጣልንበትና በፍጹም አይጎዳኝም ብለን ያረፍንበት ሰው በድንገትና ባልጠበቅነው ሁኔታ ሲጎዳን ልናገኘው እንችላለን:: ለዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ መፍትሄው አንድ ነው - ይቅርታ! አንዳንድ የጎዱህ ሰዎች አንተን ጎድተውህ እንደነበረ እንኳ የማያስታውሱበት ሕይወት ውስጥ ዘልቀው ገብተው አንተ ግን ያንን "ቂም" የተሰኘ በሽታ ይዘህ የመኖርህ መዘዝ አንተው ላይ ነው::

"ደካማው ይቅር ሊል አይችልም:: ይቅርታ ማድረግ የብርቱዎች ባህሪይ ነው" - Mahatma Gandhi

የጎዱትን ሰዎች ይቅር ለማለት የበቃ ሰው ራሱን ያሸነፈ ሰው ነው:: አንድ ሰው በአለም ላይ ለማሸነፍ ከሚያስቸግሩት ሰዎች መካከል ኃይለኛውና ከባዱ ራሱ ነው:: ታላላቅ የጦር መሪዎች፣ ባለስልጣኖች፣ የኃይማኖት መሪዎችና ጠቢባን ብዙ ሁኔታዎችንና ሰዎችን አሸንፈው በመጨረሻ ግን ራሳቸውን ማሸነፍ ሲያቅታቸው ይወድቃሉ:: ሱሰኝነት፣ ስሜታዊነት፣ አጉል ልማድ፣ የስልጣን ጥማት፣ የገንዘብ ፍቅርና የመሳሰሉትን

ራስን ማሸነፍ የሚጠይቁትን ሁኔታዎች ማሸነፍ የሚመጣው በቅድሚያ ራስን ከማሸነፍ ነው:: ከእነዚህ ራስን የማሸነፍ ብርታት ከሚጠይቁ ሁኔታዎች መካከል ስሜትን በመግዛት ሰዎችን ይቅር በማለት አልፎ የመሄድ ሁኔታ ቀዳሚው ነው::

ልምምዶችህን ስመልካም ስውጣቸው

መጎዳትህ ለተጎዱት፣ መራብህ ለተራቡት፣ መታመምህ ለታመሙት መፍትሄን የሚሰጥን ራእይ በውስጥህ ሲያስቀምጥ፣ ያን ጊዜ ከተለመደውና ለተራ ነገር ከሰከነው ሰው በልጠህ ተገኝተሃል:: "እኔ እንደተቸገርኩ እነሱም ይቅመሷት" የሚለው አመለካከት የተራዎቹ ነውና ለእነሱ ተውላቸው:: መከራ፣ ጠንካራ ወይም መራራ ያደርግሃል:: የጸሃይ ሙቀት በረዶን ሲያቀልጠውና ሲያጠፋው፣ ሲሚንቶን ግን ሲያጠነክረውና አንድን ነገር ለመገንባት እንደሚለውጠው ማለት ነው:: በመከራ የሚቀልጥና የሚጠፋ ማንነት ሳይሆን የሚጠነክርና የሚበረታ ማንነትን ለማዳበር ተግተህ አስብበት:: መነጫነጭ፣ ሰውን መውቀስ፣ ክፉን በክፉ መመለስ የትም አያደርስህም::

"ሌሎች ተራ ሕይወትን ይኑሩ፣ አንተ ግን አትኑር:: ሌሎች ባልሆነ በሆነ ይጨቃጨቁ፣ አንተ ግን አታድርገው:: ሌሎች በጥቃቅን ጉዳዮች ያልቅሱ፣ አንተ ግን አታልቅስ:: ሌሎች የሕይወታቸውን ጉዳይ ለሰው አሳልፈው ይስጡ፣ አንተ ግን አትስጥ"
– Jim Rohn

በዚህ አለም ላይ ብዙ አይነት ሰዎች ወዲህና ወዲያ ይመላለሳሉ:: ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ለሆነባቸው ክፉ ነገርም ሆነ ለሆነላቸው በጎ ነገር ምን ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው አያውቁትም:: ስለዚህ ራሳቸውን ተራ በሆነና "በመንደርተኝነት" አመለካከት ወስነውት ይኖራሉ:: ሌሎቹ ደግሞ የበሰሉና ለሁኔታዎች ሊሰጡት የሚገባቸውን ምላሽ የሚያውቁ ሆነው ሳሉ፣ ለተራ ነገር ለመስከን ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው:: አንተ ግን ከዚህ የተሸለ ማድረግ ትችላለህ:: ለተራ ነገር ከሰከኑት፣

Scanned with CamScanner

ከተጨቃጫቂዎቹና ከነጭናጫዎቹ መንደር ውጣና ወደ ስኬታሞቹ ሰፈር ግባ:: ይቻላል!

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ካለፈው ታሪክ የመፋታት እርምጃዎች:-

1. ሙሉ ሃላፊነትን ውሰድ
2. ሰዎችን ይቅር በል
3. ልምምዶችህን ለመልካም ለውጣቸው

እንዳንዶች መራራነትን፣ ጥላቻንና በአስተዳደግ ዘመናቸው የተጎነጩትን የውስጥ ቂም ይዘው ወደ አመራር ይዘልቃሉ - እንዴት አይነት ስህተት!

6

ታላላቅ ሰዎች አይወለዱም!

የምርጫ ቁልፍ

አንድ ሰው ስኬታማና ታላቅ ወይም ውዳቂና ተራ የመሆኑ ሁኔታ የሚወሰነው ከመወለዱ በፊት ነው? ታላቅነት፣ ስኬትና የተቃናለት የወደፊት ገና ስንወለድ ለእኛ ተመድበው ወደዚህች አለም እንደምንመጣ፤ ውዳቂነት፣ ስኬተ-ቢስነትና የተበላሸ የወደፊትም እንዲሁ ብለን ካሰብን እኛን ሊያነሳ የሚችል ኃይል በዚህ ምድር ላይ ተፈልጎ አይገኝም:: የሕይወት አቅጣጫ ግን የሂደትና የምርጫ ጉዳይ ነው:: ትናንት የመረጥከውን ምርጫ ዛሬ እየኖርከው ነው:: የዛሬው ውሳኔህና ምርጫህ ደግሞ የነገህን ሕይወት እየሰራው ነው:: ዛሬ የምታደርገው ነገር ሁሉ ነገ የሚበቅል ዘር ነውና!

አንዲትን ከብዙዎች ሰዎች እይታ ርቃ የምትገኝን መንደር በመጎብኘት ላይ የነበሩ ሰዎች ገና እንደደረሱ የገረማቸው የዚያች መንደር ርቀት ነው:: ከዚህ በፊት ብዙ ጎብኚዎች የመጡባት አትመስልም:: በዚህች መንደር በመዘዋወር እያሉ በአንድ ሜዳ ላይ የሚጫወቱትን ወጣቶች ቁጭ ብለው የሚያዩ አንድ አዛውንት አገኙና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንዲህ የሚል ጥያቄ ጠየቋቸው፣ “በዚህ መንደር ታላላቅ ሰዎች ተወልደው ያውቃሉ?” ጥያቄው ግልጽ ቢሆንም፣ አዛውንቱ፣ “ምን አይነት ጥያቄ ነው” በሚል እይታ ከቃኟቸው በኋላ አጅግ ቀላልና ግልጽ የሆነ መልስ ሰጧቸው:: የእኝህ

አዛውንት ፈጣን መልስ ጎበኚዎቹን አስገረማቸው። መልሳቸው፣ "በዚህች መንደር የሚወለዱት ህጻናት ብቻ ናቸው"። አስገራሚ መልስ!

"በእድል አጽንኦ አምናለሁ፣ጠንክሬ በሰራሁ ቁጥር ብዙ እድል እንደማገኝም አምናለሁ" – Thomas Jefferson

ወደዚህች ምድር በውልደት የመጣ ሰው ሁሉ የመጀመሪያ ስሙ "ሰው" ይባላል - ከዚህ ውጪ ማንነት የለም። ከሴት የተወለደ ሰው ሁሉ እኩል የመተንፈስ እድል ይዞ ነው የተወለደው። ለሁሉም የተሰጠው አንድ አስገራሚ ስጦታ "ህይወት" ይባላል። ከዚህ ውጪ ሌላ የለም። እውነት ነው፣ ብዙ ሃብት ባለበት ቤት ውስጥ የመወለድ እድል ያጋጠማቸው ሰዎች አሉ። በተቃራኒው ደግሞ በእጦት ተወልደው በእጦት ያደጉም አሉ። በሃብት ተወልደው በድህነት ኖረው የሞቱ፣ በድህነት ተወልደው ደግሞ በብልጽግና ኖረው የሞቱም ያንኑ ያህል ቁጥራቸው ብዙ ነው።

አንድ ሰው ከምን አይነት ቤተሰብ ሊወለድ እንደሚፈልግ ምርጫ ባይኖረውም ከተወለደ በኋላ ምን አይነት ጎዳና መከተል እንደሚችል ግን የመወሰን ምርጫ አለው። የትኛው ይሻላል? የአወላለድን ሁኔታ መርጦ ከተወለዱ በኋላ ለእድል ታልፎ መስጠት ወይስ የአወላለድን ሁኔታ የመምረጥ እድል ሳያገኙ ከተወለዱ በኋላ የሚሄዱበትን ጎዳና የመምረጥ እድል? እኔ ሁለተኛው ያጓጓኛል! አንድ ሰው ጾታውን፣ ቤተሰቡን፣ የቆዳ ቀለሙንና ዜግነቱን መርጦ አይወለድም ከተወለደ በኋላ ግን በእነዚህ ልዩ ስጦታዎች ተጠቅሞ ወደየት እንደሚሄድ የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው። አስፈላጊ እርምጃዎች።

እድልህን ጣስው

በዚህ አለም ላይ እድል የሚባለውን ነገር አመንነውም አላመንነው፣ በእድል የሚደመደም ነገር እንደሌለ ግን የማይለወጥ እውነት ነው። ብዙ ሰዎች ቁጭ ብለው እድልን ይጠብቃሉ - መልካም እድልን! ጥሩ ነገር ሲገጥማቸው፣ "እድለኛ ነኝ" ይላሉ።

መጥፎ ገጠመኞች ሲበዙ ደግሞ፣ "ወይ እድሌ" በማለት በእድል ላይ ይለጥፉታል። ለእነዚህ ሰዎች በእነሱ ቁጥጥር ስር ያለ ምንም ነገር የለም፣ እንዲሁ እድል እንደ ኳስ የሚጫወትባቸው ሰዎች ናቸው። እውነቱ ግን ከዚህ እጅግ የራቀ ነው። አንድን ገጠመኝ ከፉና ደግ የሚያደርገው እኛ ለዚያ ገጠመኝ የምንሰጠው ምላሽ ነው። በአንተም ሕይወት ሁኔታው ከዚህ አይለይም። እድል የሚባውን ከሃሳብህ አውጥተህ በመጣል፣ የወደፊትህን በትጋትና ትክክለኛው ውሳኔ በመወሰን ወደመኖር ማምጣት አለብህ።

"ትጋት የእድሎች ሁሉ እናት ነች" – Benjamin Franklin

ሰው ታላት ሆኖ አይወለድም፣ ሰው ከተወለደ በኋላ ነው ታላቅ ወደ መሆን የሚያድገው። ይህንንም የሚወስነው ማንነቱ፣ ዘሩ፣ የተፈጥሮ ስጦታውና አካባቢው ከፈተደለትን ሁኔታ በመነሳትና ተግቶ በመስራት ወደ ታላቅነት ለመዝለቅ ሲወስን ነው።

እድል ብቻውን ማንንም ሰው ወደከፍታ ወስዶ አያውቅም። እድልን ተጠቅመው ግን ማንነታቸውን ወደ አስገራሚ ስኬታማ ጎዳና የጨመሩ ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ቀደም ባሉት ምእራፎች ውስጥ ደጋግመን እንደተመለከትነው፣ አንዳንድ ሰዎች ምንም አይነት ምቹ ሁኔታ ውስጥ ቢወለዱም እንኳ ከተራና ከምናምንቴ ሕይወት የማለፍ ፍላጎቱም ሆነ ጥረቱ አይታይባቸውም። ሁኔታውን ከስነ-ልቦናዊ እይታ አንጻር አይተነው ብዙ ምክንያቶችን ለመደርደር ብንችልም እንኳ፣ የመጨረሻውና ዋነኛው ምክንያት ግን የግል ውሳኔ ጉዳይ ነው። ሰው፣ ሰው ለመሆን መወሰን አለበት። የአንተም ውሳኔ ይህ ሊሆን ይባል። አየህ፣ እድል ትጋትን አይወልድም። ይህ "እድል" በማለት የምንጠራው ገጠመኝ የተሰኘው ነገር በየቦታው ብቅ ጥልቅ ሲል ይታያል። እነዚህን ገጠመኞች ለሕይወታቸው እድገትና ለስኬት የሚጠቀሙ ሰዎች ግን ጥቂት ናቸው። በሌላ አባባል፣ ሁሉም ሰው በአንድ ወቅት በመንገድ ላይ ገንዘብ ወድቆ ያገኛል፣ ሁሉም ሰው ግን ያንን ገንዘብ ተገቢው ነገር ላይ አያውለውም። ገጠመኞችህን በትጋት ወደ ስኬታማ ግንባታ ስትለውጣቸው ሌሎች ገጠመኞችን ይወልዱልሃል።

ጣሪያህን ንቀሰው

ጣሪያህ ምንድን ነው? ጣሪያህ ሁኔታዎች የወሰኑልህና እንዳንተ አይነት ሰው የትም አይደርስም ብለው የደመደሙብህ እይታ ነው:: ጣሪያህ ምንድን ነው? በአንተ ሁኔታ የተወለደና ያደገ ሰው በፍጹም ከዚህ ከፍታ በላይ ሊሄድ አይችልም ብሎ ሕብረተሰቡ የደመደመው ገደብ ነው:: ጣሪያህ ምንድን ነው? ሰዎች የገቢህን ሁኔታ፣ የትውልድህን አመጣጥና የትምርት ደረጃህን ከደመሩና ከቀነሱ በኋላ የራሳቸው ድምዳሜ ላይ በመድረስና መስመርን በማስመር በላይህ ላይ የከደኑት ከዳን ነው:: አየህ፣ ሕብረተሰቡ ይህንን የማድረግና "ከዚህ አታልፍም" ብሎ መስመር የማስመር መብቱ የተጠበቀ ነው:: አንተም በበኩልህ ያንን መስመር አልፈህ የመሄድ ሙሉ መብት አለህ:: ያለፈው ትውልድ ያቆመበት ላይ ማቆም የለብህም፣ አዲስ ፈር ልትቀድድና ወደ አዲስ አቅጣጫ ልትዘልቅ ይገባሃል:: ይህ እንዲሆን ግን "ባለሁበትና ሰዎች ነህ ብለው በወሰኑልኝ ሁኔታ አልወሰንም" የሚል ቁርጥ ውሳኔ ከአንተ ይጠበቃል::

"ውስንነትህን ለይተህ እወቅ፣ ነገር ግን በፍጹም አትቀበለው" – Unknown Source

ይህንን አትዘንጋ፣ ወደዚህች አለም ስትመጣ ብትወድም ባትወድም ከሁለት ነገሮች ጋር ትወለዳለህ - ከብርታትና ከድካም ጋር:: ብርታቶችህ፣ የሚሳኩልህ፣ የሚያዳጉህና ብታሳድጋቸው ለስኬት የሚያበቁህ ናቸው:: ድካሞችህ ደግሞ ብዙም የማያዳጉህ፣ ለማድረግ ስትሞክራቸው እጅግም የማይሳኩልህና የሚያታግሉህ ነገሮች ናቸው:: የዚህን እውነታ ከመቀበል በላይ ምንም ምርጫ የለህም:: አብዛኛው የሕብረተሰቡ ክፍል ካለማቋረጥ ድካምህንና ውስንነትህን ነው የሚያሳይህ:: ያንንም ድካምህን ከጠቆመህ በኋላ ከዚያ ነገር የተነሳ የትም መድረስ እንደማትችል ይነግርሃል:: እውነቱን ነው! በድካምህና በማትችለው ነገር ተጠቅመህ ውስንነትህን አልፈህ መሄድና ማደግ አትችልም:: ማተኮር ያለብህ ብርታትህ ላይ ነው:: አእምሮህ የተከፈተለትንና ብርቱ ጎንህን በማዳበር ካለህበት ሰፍራና የውልደት ሁኔታ አልፈህ ለመሆን ወደተፈጠርከለት

ማንነት ማደግ ትችላለህ:: ይህንን አትርሳ፣ በዚህች ምድር ላይ አንድ የምታድግበትና የምትለመልምበት ቦታ አለህ!

የወደፊትህን ፍታው

የወደፊትህን የምትፈታበት ዋነኛ መንገዱ ካለፈው ታሪክህና ከአመጣጥህ ሁኔታ በመፋታት ነው:: ካለፈው ታሪክህና ከአመጣጥህ ጋር ሊኖርህ የሚገባ ብቸኛ ግንኙነት ከእሱ የምታገኘውን ትምህርት በመቅሰምና መልካም አመጣጥህ ላይ በመገንባት አቅጣጫ ሊሆን ይገባዋል:: የዛሬ ዓመት፣ የዛሬ ሶስት ዓመት፣ የዛሬ አምስት ዓመት እና የዛሬ አስር ዓመት ልትሆን የምትፈልገውን የውስጥ እይታህን በጽሑፍ ላይ አስፍረው:: በመቀጠልም ይህንን ሁኔታ እውን ለማድረግ መውሰድ የሚገባህን እርምጃዎች በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም የጊዜ ገደቦች የግብ ደረጃዎች አስቀምጣቸው:: በመጨረሻም በእጅህ ባለው ነገር ተንቀሳቀስ:: ፈጠነም ዘገየም ወደ አሰብከበት ደረጃ መድረስህ የማይቀር ነው::

"ተሸናፊዎች በትናንትና ውስጥ ይኖራሉ:: አሸናፊዎች ግን ከአለፈው በመማር፣ በዛሬዋ ቀን ላይ ሆነው በደስታ ለወደፊቱ ይሰራሉ" – Denis Waitley

ብዙ ሰዎች የሚኖሩት በትናንትናው ታሪክ ነው:: አንዳንዶቹ ትናንት ያከናወኑትን "ጀግንነት" እና "ገድል" በመቁጠር ቁጭ ብለው ሲያወሩትና ሲተርኩት ይኖራሉ:: ይህንንም በማድረጋቸው ጊዜአዊ የውስጥ እርካታ ከማግኘት ያለፈ ሌላ ምንም ጥቅም አያገኙም:: ለእነሱ ስኬት ማለት ይህችው ነች - አሳዛኝ ሁኔታ! ሌሎቹ ከዚህ ይልቅ አሳዛኞቹ ደግሞ ያለፈውን ውድቀትና አለመሳካት በመቁጠር ሲያማርሩና ሲነጫነጩ እድሜአቸውን ያሳልፋሉ:: አሸናፊነትህንና ተሸናፊነትህን የሚወስነው ግን ትናንት ያሳለፍከው መልካም ወይም ከፉ ልምምድህ አይደለም:: ጉዳዩ ያለው ያለፈውን መልካሙንና ከፉውን ገጠመኝ ተጠቅመህ አዲስ የወደፊት ለመገንባት የመነሳትህ ሁኔታ

Scanned with CamScanner

[illegible]

[illegible]

1. [illegible]
2. [illegible]
3. [illegible]

አንድ ሰው ከምን አይነት ቤተሰብ ሊወለድ እንደሚፈልግ ምርጫ ባይኖረውም ከትዳሩ በኋላ ምን አይነት [illegible] እንደሚችል ግን የመጠገን ምርጫ አለው::

7

"ሠስ'ንነቴ ሳይ ስተኩሬ ስሳውቅም"

ብርታት ላይ የማተኮር ቁልፍ

በሕይወታችን ያጋጠሙን ተግዳሮቶች በወደፊት እርምጃችን ላይ ምን ተጽእኖ አላቸው? ሁለት ሰዎች በአንድ አይነት ተግዳሮት ውስጥ ራሳቸውን አግኝተውት፤ አንደኛው እልፎት ሲሄድና ወደተፈጠረለትና በአይነ-ህሊናው ወዳየው ግብ ሲዘልቅ፤ ሁለተኛው ግን ሲያዘቅጥና በሁኔታው ሲመታ ሲታይ ምስጢሩ ምንድን ነው? የአንድን ሰው ሁኔታ የሚወስነው በዙሪያው ወይም በእርሱ ላይ የሆነው ነገር ሳይሆን በውስጡ የሆነው ነገር እንደሆነ ማስተዋል አይከብድም:: አካልህን፤ የኢኮኖሚ ሁኔታህንና ቤትህን የነካው አሉታዊ ነገር ውስጥህን ካልነካው ምንም አትሆንም::

"በሁለት ሰዎች መካከል ቆሜ ከንፈራቸውን በጣቶቼ ስነካ ምን እንደሚያደርጉ ግር ስለሚለኝ ውስጤ ያዝን ነበር:: እኔም እንደነሱ ካለምንም ውጤት ከንፈሬን አንቀሳቅስ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ሁኔታው በጣም ስለሚያበሳጨኝ ሰውነቴ እስኪዝል ድረስ እጮህና ያገኘሁትን ነገር ሁሉ አደበድብ ነበር::" እነዚህ ቃላቶች ገና ሁለት ዓመት ሳይሞላት ማየቷንና መስማቷን ያጣችው የሄለን ኬለር ቃላቶች ናቸው - በጽሑፍ

የገለጸቻቸው ቃላቶች፡፡ ገና በ19 ወሯ በደረሰባት የትኩሳት በሽታ ራሷን የሳተችው ሄለን፣ ወዲያውኑ የማየቷንና የመስማቷን ብቃት ተነጠቀች፡፡ ስለሄለን ስናስብ የሚያስገርመን ማየትና መስማት የተሳናት ሴት መሆኗ አይደለም፡፡ በሁኔታዋ ሳትበገር የመጀመሪያዋ ማየትም መስማትም የማትችል የዲግሪ ተመራቂ፣ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ ጸሃፊ፣ ...ለመሆን መብቃቷ ያስገርመናል!!! ለዚህ ያበቃትን አመለካከቷ በአጭር ቃል ስታስቀምጠው፣ "ውስንነቴ ላይ አተኩሬ አላውቅም፣ ልቤንም በኃዘን አይሞሉትም፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንድ ናፍቆቶች ቢመጡብኝም በአበባዎች መካከል እንደሚነፍስ ለስላሳ አየር እጅግ በጣም ስስ ስሜቶች ናቸው"፡፡

"የራስን ሁኔታ እያዩ ሲያዝኑና ከንፈር ሲመጥጡ መኖር ከፉ የተባለው ጠላታችን ነው፡፡ ለዚህ ጠላት ራሳችንን አሳልፈን ከሰጠነው በዚህ ዓለም ውስጥ ምንም ጥበብ የሞላው ነገር ማድረግ አንችልም" – Hellen Keller

ጎደለኝ የምትለው ነገር ምንድን ነው? ምን ቢኖርህ የተሳካ ህይወት የምታገኝ ይመስልሃል? የትኛውስ ጎዶሎህ ቢሞላ ከዚህ የተሻለ ህይወት የምትኖር ይመስልሃል? አንድን እውነታ ላስታውስህ - አንተ "ጎዶሎዬ ይህ ነው" ብለህ የምታስበው፣

እንዲያውም ከዚያ የከፋ ሁኔታ ውስጥ እያለ የተሟላ ሕይወት የሚኖር ሰው እንዳለ! በአንጻሩም ሌላ እውነታን ወደ አእምሮህ ልዝራ፣ በዚህ ምድር ሙሉ፣ ስኬታማና ደስተኛ ሆኜ ለመኖር ይህኛውና ያኛው ያስፈልገኛል ብለህ የምታስባቸውን ነገሮችና ከዚያም በላይ እያላቸው በጣም አሳዛኝ ሕይወት የሚኖሩም ሰዎች እንዳሉ - ላስታውስህ፡፡ የአንተን ስኬት የሚወስነው ያለህና የሌለህ ነገር፣ ወይ ደግሞ የተቀማኸው መልካም ነገርና የደረሰብህ ጉዳት አይደለም፡፡ የግልህን ሁኔታ እያየህ ለራስህ ከንፈርህን በመምጠጥ የምትኖር ሰው ከሆንክ እጅግ አሳዛኝ ሰው ነህ፡፡ ከዚህ ሁኔታ ለመላቀቅ፣ ራስን በራስ ከማስተዛዘን ዝንባሌ መውጣት አለብህ፡፡

ከሆነብህ ጤና ቢስ ነው ከምትለው ገጠመኝ አልፈህ እንድትሄድ የሚረዱህ እውነታዎች ከዚህ በታች ሰፍረውልሃል፡፡ እነዚህ ነጥቦች ከላይ ታሪኳን በጥቂቱ ከተመለከትነው ከሄለን ኬለር አንደበት የወጡ የጥበብና የተሰፉ ቃላቶች ናቸው፡፡

ከእውነታው አትሽሽ

ከላይ ታሪኳን የተመለከትነው ይህች አስገራሚ ሴት፣ ሄለን ኬለር ሁኔታዋን ስታስበው፣ የምትደርስበት የመጨረሻ ድምዳሜ ማየትም መስማትም አለመቻሏን ነው፡፡ አይታን አይታው አታውቅም፣ መስማትንም ሰምታው አታውቅም (ከህጻንነቷ ጀምሮ)፡፡ ይህንን እውነታ ከመሸሽ ይልቅ አውጥታና አውርዳ፣ በሚገባም አስባና ድምዳሜ ላይ ደርሳ ሁኔታዋን መቀበልን መረጠች፡፡ ሁኔታዋን መቀበል ብቻም አይደለም፣ ሁኔታዋ ለተሻለ ነገር ለመለወጥም ቆረጠች፡፡ በዚህም ውሳኔዋ ማየትና መስማት ከሚችሉ ከብዙ ሰዎች ይልቅ የተሻለን ነገር አከናውና አለፈች፡፡

"ሰዎች ማሰብ አይፈልጉም፡፡ አንድ ሰው ማሰብ ሲጀምር ያ ሰው ወደ አንድ ድምዳሜ መድረሱ አይቀርም፡፡ በአንድ ነገር ላይ የምንደርስበት የእውነታ ድምዳሜ ሁል ጊዜ አስደሳች አይደለም" – Hellen Keller

ሰዎች በሕይወታቸው ያለውን እውነታ መጋፈጥ አይፈልጉም፡፡ አይናቸውን ጨፍነው ሁኔታዎቹ እንደሌሉ ማሰብን ይፈልጋሉ፡፡ ሁኔታቸውን በሚገባ ቢያጠኑት የሚደርሱበት እውነታ ከሁለት አያልፍም - በአንድ ጎኑ የደረሰባቸው ሁኔታ ሊለውጡት የማይችሉትንና "ቋሚ" የሆነን ጉዳት አድርሶባቸው ራሳቸውን ያገኙታል፡፡

በሌላ ጎኑ ደግሞ የደረሰባቸውን ገጠመኝ በመታገልና በማሸነፍ ወደነበረበት ወይም ቀድሞ ከነበረበት ወደተሻለ የመለወጥ እድሉ ይኖራቸዋል፡፡ ሁኔታው ይህም ሆነ ያኛው፣ አንድ ሰው ምንም አይነት ምላሽን ለመስጠት በመጀመሪያ ማሰብ አለበት፡፡ ከአንተም የሚጠበቀው ይህ ነው - ያለህበትን ሁኔታ በመሸሽ፣ ስለእርሱ ባለማሰብና እንደሌለ

Scanned with CamScanner

አድርገህ ለመቁጠር በመሞከር የትም አትደርስም፡፡ እውነታው እውነታው ነው፤ ከእውነታው ባሻገር ግን ሊፈጠር የሚችል አስገራሚ አለም አለ፡፡ ወደዚያ አለም ገስግስ፣ በአንተ ሁኔታ ተሰርቶ ያልታወቀን ነገር ለመስራት ራስህን አበርታ፡፡

ቀና ብለህ ሂድ

ሄለን ኬለር አንገቷን አቀርቅራ እንድትሄድ የሚገፉፋት በቂ ምክንያት ነበራት - ሰው በፍጹም ማጣት የማይፈልጋቸውን ሁለት ነገሮች ወደማጣት መጥታለች፡፡ እርሷ ግን እምቢ አለች፡፡ ካለችበት ሁኔታ ውስጥ ድፍረትን የሚጠይቁ ድንቅ ነገሮች ለማከናወን ቆርጣ ተነሳች - አደረገችውም፡፡ መሸነፍን፣ አንገት ደፍቶ መሄድን፣ ለራስ ከንፈር ሲመጥጡ መኖርንና በሰዎች ላይ ማማረርን እንደምርጫ አልወሰደቻቸውም፡፡ በዚህም ውሳኔዋ ከፉ ልምምዷ ያስቀመጠባትን ጫና ጥላ ነጻነቷን በማወጅ ወደፊት ገሰገሰች፡፡

"አንገትህን በፍጹም አታቀርቅር፡፡ ሁል ጊዜ ቀና በል፡፡ ይህችን አለም አይን አይኗን ተመልከተሃት በድፍረት ኑር" – Hellen Keller

ምን አንገት የሚያስደፋ ነገር አለብህ? የደረሱብህን ሁኔታዎች ስታስባቸው አቅም እንድታጣ የሚያደርግህ የትኛው ነው? ሰው ፊት እንዳትቀርብ፣ የልብ ወዳጅ እንዳትይዝና ገለል ብለህ ድብቅ ሕይወት እንድትኖር የሚጎትትህ ጤና ቢስ ገጠመኝህ የትኛው ነው? ያለህ ነገር ሌላው ሰው ካለው ነገር ቢያንስም እንኳ፣ ሰው መሆንህ ግን ከማንም አያንስም፡፡ ክብር ያለው ሰው የመሆንህ ጉዳይ የሚወሰነው ለራስህ በሰጠኸው ክብር ነው፡፡ የገጠሙህን ሁኔታዎች ተጋፈጣቸው፣ ቀና ብለህ ለመኖርም ወስን፡፡ በዚህች ምድር ላይ ያለ ጀግና እስካሁን ምንም ከፉ ያልገጠመው ሰው አይደለም፣ ጀግናው ከገጠመኞቹ አልፎ የሚሄደው ሰው ነው፡፡

ይህ ጀግንነት የሚለካው በመፎከርና "ከማን አንሳለሁ" በማለት ሳይሆን ያመኑበትን እውነት ትህትና በተሞላበት ጥንካሬ በመወጣት ነው፡፡

ከአንተ የባሱትን አስብ

ሄለን ኬለር ከምትታወቅበት ዝንባሌዋ አንዱ ከእርሷ የከፋ ሁኔታ ደርሶባቸዋል የሚባሉትን ሰዎች በማሰብና ለእነሱ የተሰፋ ጭላንጭል በመሆንዋ ነው፡፡ የሆነባትን ሳይሆን ያልሆነባትን ከዚያ የከፋ ነገር መቁጠርና "ተመስገን" ማለትን መረጠች፡፡ የደረሰባትን ከፉ ልምምድ ሳይሆን የደረሰላትን መልካም ገጠመኝ ለማሰላሰል አእምሮዋን ከፈተች፡፡ ይህ አይታዋ ነው የደረሰችበት ታላቅ ደረጃ እንድትደርስ የደገፋት፡፡ መጣልን ጣለችው፣ ተስፋ መቁረጥን ተስፋ አስቆረጠችው፣ መገፋትን ገፋችው፣ ማንነቷንና መለወጥ የማትችላቸውን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ እውቅና በመስጠት ተቀበለቻቸው፣ ወደፊትም ሄደች፡፡

"የእኛን ሁኔታ ከእኛ የተሻለ ነገር አላቸው ከምንላቸው ሰዎች ጋር ከማወዳደር ይልቅ፣ በተግዳሮት ውስጥ ካሉት ከብዙሃኑ ጋር ብናወዳድረው ምን ያህል ከታደሉት መካከል እንዳለን ይገለጥልናል"– Hellen Keller

አንድ ቀን ያልበላው ሶስት ቀን ያልበላ ሰው እንዳለ ቢያስብ፤ በኪራይ ቤት የሚኖረው በመንገድ ስለሚያድረው ሰው ቢያስታውስ፤ የታመመው በህይወት የመኖር እድል ያላገኘውንና ካለአድሜው የተቀጨውን ቢያስታውስ አይታውን እንዴት ያሰፋው ነበር? ለጥቂት ደቂቃ ይህንን ጽሑፍ ማንበብህን ቆም አድርግና ያለህበት አስከፊ ነው የምትለውን ሁኔታ እስቲ አስበው፡፡ ከዚያም በመቀጠል፣ ከአንተ ሁኔታ የባሰ ነገር ላይ ያሉትን ሰዎች ደግሞ አነጻጽር፡፡ እስኪገርምህ ድረስ ምን ያህል ደህና እንደሆንክ ይበራልሃል፡፡ ይህ ማለት ምንም ነገር አልደረሰብህም ማለት አይደለም፡፡ ወይም ደግሞ ከደረሰብህ ሁኔታ የተነሳ ምንም አላመመህም፣ ውስጥህም አልተጎዳም ማለት አይደለም፡፡ እውነታው - ነጻ የሚያወጣህ እውነታ - ከአንተ የከፋ ነገር የደረሰባቸው ሰዎች እንዳሉ በማሰብና ከዚህ የከፋ ሁኔታ ሊደርስብህ ይችል እንደነበር በመገንዘብ ለብሩህ የወደፊት የመስራት አስገራሚ እውነታ ነው፡፡ ትችላለህ!

Scanned with CamScanner

በዚህ ምእራፉችን የተመለከትናቸው ብርታት ላይ የማተኮር ቁልፎች:-

1. ከእውነታው አትሸሽ
2. ቀና ብለህ ሂድ
3. ከአንተ የባሱትን አስብ

> የግልህን ሁኔታ እያየህ ለራስህ ከንፈርህን በመምጠጥ የምትኖር ሰው ከሆንክ እጅግ አሳዛኝ ሰው ነህ::

፰

የነፉሱ ግፊያ ወደ ከፍታዬ ያወጣኛል

ተግዳሮትን ለአላማ የመጠቀም ቁልፍ

በዚህ ብዙ እንቅፋቶች በሞሉበት ዓለም ውስጥ እንዴት በስኬታማነት መኖር ይቻላል? ይህ የብዙዎች ጥያቄ ነው:: ተግዳሮት የሁሉም እጣ ነው፣ ያንን አልፎ መሄድ ግን ለአስተዋዮች ብቻ የተቀመጠ ነው:: እንቅፋት፣ ግፊያ፣ አለመሳካት፣ የሰው ክፋት፣ ክስረት፣ የጤና ቀውስ፣ ያልተጠበቀ፣ ድገተኛና አስደንጋጭ ነገር ... ሰው በዚህ አለም ሲኖር ልቡን የሚያዝሉና የሚጋፉት ሁኔታዎች እጅግ ብዙ ናቸው:: አስተዋይ ሰው፣ የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ሁሉ ለስኬታማነት ሊጠቀምበት እንደሚችል የገባው ሰው ነው:: ለመውደቅ የተዘጋጀው ግን በገፋው ነገር ሁሉ የሚገፋና ከወደቀበት የማይነሳ ሰው ነው::

ንስር! አስገራሚ ፍጡር! ማን ይይዘዋል? ማን ይደርስበታል? እርሱ የሚወጣው ከፍታ ድረስስ ማን ሊወጣ ይችላል? ንስርን የሚጋፋው አንድ ብቸኛ ተግዳሮት ነፋስ ነው:: የሚያስገርመው ነገር ግን ንስር ወደ ከፍታው እንዲወጣ የሚደግፈውም ያው የሚጋፋው ነፋስ የተሰኘው ነገር ነው:: የንስር አቋም - "የሚጋፋኝን ይህንን ነፋስ ተጠቅሜ ወደከፍታዬ አበርራለሁ፤ የነፋሱ ግፊያ ወደ ከፍታዬ ያወጣኛል":: ንስር ከሚጋፋው ብቸኛ ጠላቱ ከነፋስ ተግዳሮት ውጪ ለመኖር ቢወስንና ያንን ጥያቄውን ተግባራዊ

የሚያደርግለት ኃይል ተገኝቶ ነፋስ ከፍጥረት ከስተት ውስጥ ቢወጣለት፣ የሚጋፋው ብቸኛ ነገር ስለተወገደለት "እፎይ" ይላል:: ታሪኩ ግን እዚያ ላይ ብቻ አያበቃም:: የከፍታ ሕይወቱንም እዚያው ያስረክባል:: ከሚጋፋው ከብቸኛ ጠላቱ ከነፋስ ውጪ ንስር ከዶሮ ተለይቶ አይታይም:: ለንስር የከፍታው ምስጢር ተግዳሮቱ ውስጥ ተሰውሮ ይገኛል:: ነፋስ ንስርን ይገፋዋል፣ ለነፋሱ ከሚሰጠው የንስር ምላሽ የተነሳ ግን ንስር ወደ ላይ ይገፋለታል:: ነፋስ በፍጹም ንስርን ገፍቶ ምድር ላይ አስቀምጦት አያውቅም::

"የሕይወት ተግዳሮቶች መራመድ እስከማትችል ድረስ ሊያስሩህ ሳይሆን እንተነትህን የበለጠ እንድታውቀው ሊረዱህ ይገባል" – Bernice Johnson

የሰውን ዘር የአምፖልን ብርሃን እንዲፈለስፍ ያነሳሳው የጨለማው ተግዳሮት መሆኑን አትዘንጋ:: የበሽታው ግፊያና የስቃያችን ጥልቀት በህክምና ዛሬ የደረስንበት ደረጃ እንድንደርስ አበረታን:: የመራራቃችንና ለመገናኘት ያለን ናፍቆት የጫነብን የመገለል ጫና የበረራን ፈጠራና የስልክን መስመር የመሳሰሉትን ብልሃቶች ከውስጣችን ፈልቅቆ አወጣው::

የሙቀቱ ግለት የአየር ማቀዝቀዣን እንድንፈልግ አደረገን:: የብርዱ ጭካኔ፣ የአየር ማሞቂያን ፈልገን እንድናገኝ አስገደደን:: እነዚህ ነገሮች ከዚህ በፊትም ነበሩ፣ ከእይታችን ግን ተሰውረው ነበር:: ለዚህ ነው አዳዲስ ግኝቶች "ግኝት" የሚባሉት፤ ተደብቀው የነበሩ፣ አሁን ግን በቆረጡና በፍላጋቸው በጸኑ ሰዎች የተገኙ! ምስጢሩ ግን ይህ ነው - ተግዳሮቶቹ ባይኖሩ ግኝቶቹ ወደመሆን ባልመጡ! "የአንድ ነገር እጥረት የአዳዲስ ግኝቶች እናት ነች" እንደሚባለው ማለት ነው:: በሕይወትህ ያለብህን ትግልና ግፊያ በዚህ መልኩ እስከታየው ድረስ ወደከፍታ መብረር የህልም እንጀራ እንደሆነብህ ትኖራለህ:: ይህ እንዳይሆን ልትገነዘባቸው የሚገቡህን እውነቶች ላስታውስህ::

ተግዳሮት የማደጊያህ መንገድ እንደሆነ አስታውስ

ከለማቋረጥ ስፖርትን የሚሰሩ ሰዎች የሰውነታቸው እንደዚያ መፈርጠም ምስጢር ያለው ጡንቻቸውን ቀድሞ ከሚችለው የበለጠ ውጥረት ውስጥ በመጨመር ነው:: ይህ የከብደት ተግዳሮት ጡንቻው እንዲወጠርና እንዲጎዳ ያደርገዋል:: ይህ የሰውነት ክፍል በደረሰበት ውጥረት የተጎዳውን ክፍል ከቀድሞው የበለጠ አጠናክሮ ይጠግነዋል:: ይህ ተጠናክሮ የተጠገነ የሰውነት ክፍል "ጡንቻ" ይባላል:: የማንነትህም ጉዳይ ከዚህ ተለይቶ አይታይም:: እያንዳንዱ የሚገጥምህ ውጥረት ማንነትህን ለበለጠ ነገር እንዲዘጋጅ ያደርገዋል:: በዚህ ሁኔታ የሚያድገው ማንነትህ የስሜት ጽንአት፣ የፈጠራ ብቃትንና ከተግዳሮት አልፎ የመሄድን ማንነት ውስጥህ ይገነባል::

"ሕይወት በጣም ያጓጓል:: አንድ አንድ ስቃዮችህ በስተመጨረሻው የብርታት ምንጭ ይሆኑልሃል" - Drew Barrymore

ምናልባት ከዚህ በፊት ደጋግመህ ክትባት ወስደህ ታውቃለህ ብዬ እስባለሁ:: በወሰድከው ክትባት ውስጥ የጤናው ባለሞያ እንዳያጠቃህ የታሰበውን በሽታ በጥቂቱ ወደ ሰውነትህ ውስጥ ይጨምረዋል:: ሰውነትህ የደረሰበትን ድንገተኛ ወረራና ተግዳሮት ለመቋቋም የሚያወጣቸው አቋሞች ሰውነትህን በግሩም የመከላከያ ኃይል ይገነባዋል:: ስለዚህም ይህ በክትባት መልክ አስቀድሞ ለሰውነትህ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው የበሽታ አይነት ሲመጣ ለማንነትህ እንግዳ ስላልሆነ በቀላሉ በቁጥጥር ስር ያውለዋል::

የዛሬ ተግዳሮትና ስቃይ፣ የነገ የብርታት ምንጭ! ይህንን እይታ ካላዳበርክ ለጥቅምህና ለእድገትህ የሆኑትን ነገሮች በመቋቋም ወይ ባለህበት ትቀራለህ ወይም ደግሞ ወደ ኋላ ታዘቅጣለህ::

Scanned with CamScanner

ተግዳሮትህን ስጥቅምህ ተጠቀምበት

ተግዳሮትህን እንደ እድል መቁጠር መጀመር አለብህ - አዲስ እይታን የማግኛ እድል! ይህ የሚያጓጓ ሃሳብ አይደለም ነገር ግን ስኬታማ ሰዎች ራሳቸውን የቃኙበት አመለካከት ነው:: ለምሳሌ፣ የመሬት ስበት ሁኔታ ደስ የሚያሰኝ ነገር አይደለም:: ከመሬት ተነስተህ የትም እንዳትሄድ አፍኖ የያዘህ ጉዳይ ነው:: ይህንን ሁኔታ ግን ለብዙ ጥቅም ማዋል ተችሏል:: ለምሳሌ፣ በውኃ ኃይል የሚፈጠሩ የኤሌክትሪክ የኃይል ምንጮች ከመሬት ስበት ጋር በሚደረግ ትብብር ወደመሆን የሚመጡ ናቸው:: ተግዳሮት ሁሉ ጥቅም አለው:: ተግዳሮቱ የሚያመጣውን ችግር የመቆጣጠርና በተግዳሮቱ ተጠቅሞ ወደተሻለ ነገር የመዝለቁ ውሳኔ ግን አንተ ጋር ነው ያለው:

"ሰውን ሰው ከሚያደርጉት ልዩ ነገሮች መካከል አንዱ እንቅፋቶችን ወደ መልካም ገጠመኞች የመለወጥ ብቃቱ ነው" – Eric Hoffer

ብቸኝነትህን የማንበቢያና ራስን የማሻሻያ ነጻ ጊዜ እንዳገኘህ በመቁጠር በእውቀት ለማደግ ተጠቀምበት:: ለታክሲ ገንዘብ አለማግኘትህን በእግር ጉዞ የሚገኘውን የጤንነት ጥቅም ያዝበት:: እንደሌሎቹ ሰዎች በፈለግከው ጊዜ በየምግብ ቤቱ መብላት አለመቻልህን በቤትህ ጤናማ ነገርን ሰርተህ በመብላት የሚገኘውን የጤንነት እርግጠኝነት በማሰብ ተጠቀምበት:: "ተግዳሮት" የተሰኘውን ቃል አዲስ ትርጉም እንድትሰጠው አበረታታሃለሁ:: ተግዳሮትን እድገት ብለህ ጥራው:: ተግዳሮትን የአዲስ እይታ እድል ብለህ ሰይመው:: "እድሌ ጠማማ ነው፣ ደሜ መራራ ነው" የሚሉትን ስትሰማ ያደግሃቸውን ቅኝቶች ለውጣቸው:: በምትኩ የተስፋና የስኬት ቅኝቶችንና ግጥሞችን ደርስ:: ለራስህና ለወደፊቱ ትውልድ የሚያስገርምን የእይታ አለም ታስተዋውቃለህ::

ችግርህን በተለያየ መልኩ ለጥቃው

አንድን ነገር ሞክሮ ግፊያው ሲበዛ ስብር የሚል ሰው የበዛበት አካባቢ እንዳደከ አትዘንጋ:: አንዴ ሞክሮ አልሆን ሲለው ዘወር በማለት ነገሩ ያልሆነበትን ምክንያት ማውራትና መነጫነጭ ወይም ደግሞ የሚወቀስ ሰው ፍለጋ የሚቀናው ሕዝብ ብዙ ነው:: ብዙ ችግሮች ግን በአንዴ አይፈቱም:: በአንዱ መንገድ አልሆን ያለውን በሌላ አቀራረብ በማጥቃት ግን የማይፈታውን መፍታት ይቻላል:: አለቱ ከተለያየ አቅጣጫ ብዙ ከመደብደቡ የተነሳ ይሰነጠቃል:: ገመዱ በግራና በቀኝ ከመገዝገዙ የተነሳ ይበጠሳል:: ጥቂቷ የዝናብ ጠብታ ደጋግማ ከመንጠባጠቧ የተነሳ ጠንካራውን ነገር ትቦረቡረዋለች:: በመደጋገም፣ አዲስ መንገድን በመፍጠርና ባለማቋረጥ ለሌላው እምቢ ያለ ለአንተ እሺ ይልሃል! ይህ እንዲሆን "እምቢታን" እንደ መጨረሻ መልስ ላለመቀበል መቁረጥ አለብህ:: ውስጥህን ግን ብታበረታውና ተጋግጬተህ በተመለስከ ቁጥር፣ "አይዞኝ" በማለት እንደገና ብትሞክር የምታስገርም ሰው ሆነህ ራስህን ታገኘዋለህ:: የራስህን ከብረ-ወሰን ከመስበር አንጻር መሮጥ ትጀምራለህና::

"ተግዳሮቶችህን በመጋፈጥና አቋም በመያዝ ለመፍትሄ አንድን ነገር አድርግ:: ያሰብከውን ያህል ከባድ እንዳልሆኑ ይገለጥልሃል" - Norman Vincent Peale

ከዚህ በፊት በሌላ ሰው ላይ ደርሶ የማያውቅ ችግር በፍጹም ሊገጥምህ አይችልም:: ከዚህ በፊት በሌላ ሰው ላይ ደርሶ የማያውቅ ችግር በፍጹም ሊገጥምህ አይችልም::

አስተሳብህ ውስጥ ብቻ ነው:: ከአስተሳሰብህ ውስጥ እምቢ በማለት ያስወጣኸው የአለመቻል ስሜት ወዲያው ይሞታል::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ተግዳሮትን ለአላማ የመጠቀም ምክሮች:-

1. ተግዳሮት የማደጊያህ መንገድ እንደሆነ አስታውስ
2. ተግዳሮትህን ለጥቅምህ ተጠቀምበት
3. ችግርህን በተለያየ መልኩ አጥቃው

ከሚጋፋው ከብቸኛ ጠላቱ ከነፋስ ውጪ ንስር ከዶሮ ተለይቶ አይታይም::

9

ሞት ነጋዴው ሞተ

የዘላቂነት አመለካከት ቁልፍ

ከዚህ ዓለም ሳልፍ ሰዎች በምን እንዲያስታውሱኝ እፈልጋለሁ? ከእኔ በፊት የነበሩት ሰዎች እንዳለፉ ሁሉ፣ እኔም ነገ ማለፌ ካልቀረ ካለፍኩ በኋላ ሰዎች በምን እዲያስታውሱኝ እንደምፈልግ የመወሰኛው ጊዜ አሁን ነው:: አንዳንድ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ያላቸውን ሕይወት ለእነሱ ብቻ በተመቻቸው መንገድ እስከኖሩ ድረስ ካለፉ በኋላ ሰዎች ስለእነሱ የሚያስቡት ነገር ትርጉም እንደሌለው ያስባሉ:: ሌሎች ደግሞ በዚህ ምድር ላይ የኖሩት ኑሮ ለዓመታት የሚቆይን ተጽእኖ ጥሎ እንደሚያልፍ በማሰብ ጥንቃቄ የሞላውን ሕይወት ለመምራት ይጥራሉ:: የሚያስገርመው እውነት፣ ሰዎች ስለእኛ የሚያስቡትን ትክክለኛውን ሃሳባቸውንና እይታቸውን በግልጽ የሚናገሩት እኛ ካለፍን በኋላ መሆኑ ነው::

ከመቶ አመታት በፊት አንድ ሰው የዕለቱን ዜና ለማንበብ ጋዜጣውን ሲዘረጋ አንድ አስደንጋጭ ነገር አነበበ:: በዚያ ጋዜጣ አንድ አምድ ውስጥ የራሱን ስም ተመለከተና ግራ ገባው:: በእለቱ ጋዜጣው ሊዘግበው የፈለገው የሌላን ሰው ሞት ሆኖ ሳለ በስህተት ግን የእርሱን ስምና ታሪክ አስፍሮ ነበር:: በርእስ አንቀጹ ከተጻፉት ጽሑፎች መካከል እንዲህ የሚሉ ሃሳቦች ይገኙበታል - "የዳይናማይትና የቦምቡ ንጉስ . . . የሞቱ ነጋዴ

Scanned with CamScanner

ሞተ" ይላል፡፡ ጽሑፉ ላይ፣ "ይህ ሰው ሚሊየነር የሆነው ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚገዳደሉበትን ነገር በመፈልሰፍና በመሸጥ ነው" ይላል፡፡ ይህ ሰው አልፍሬድ ኖቤል (Alfred Nobel) ነው - ዳይናማይትንና ሰዎች ለጦርነት የሚጠቀሙበትን የፈንጂ ንጥረ ነገሮች የፈለሰፈ የስዊድን ሳይንቲስት፡፡ የሞተው ሌላ ሰው ነው፣ ጋዜጣው ግን በስህተት የእሱን ታሪክ ነበር የጻፈው፡፡ ኖቤል ያንን ጽሑህ ካነበበ በኋላ እጅግ ደነገጠ፡፡ ለራሱ እንዲህ ሲል ነገረው፣ "ለካ ስሞት ሰዎች በዚህ ሁኔታ ነው የሚያስታውሱኝ? ...ህይወቴን ለመልካም ነገር በማዋል ማሳለፍ አለብኝ"፡፡ ኖቤል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አመለካከቱ እንደተለወጠ ይነገራል፡፡

ኖቤል ፕራይዝ በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በህክምና፣ በስነጽሑፍ፣ በሰላምና በሳይንስ የላቀ ስራ ላበረከቱ ሰዎች የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡ ይህ ሽልማት ከተጀመረበት በፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ1901 ጀምሮ 2010 ድረስ 543 ጊዜ ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ ለምሳሌ፣ ኮፊ አናን፣ ጂሚ ካርተር፣ ዴዝሞን ቱቱ፣ ማርቲን ሉተር፣ ማዘር ትሬሳና ባራክ ኦባማ የዚህ ሽልማት ተቀባዮች ናቸው፡፡ ኖቤል ከዚህ አለም በሞት ሲለይ በሚልየን የሚቆጠር ዶላር ለዚሁ ሽልማት እንዲውል ኑዛዜ አድርጎ ነው የሞተው፡፡

"ሁላችንም እንሞታለን፡፡ ግባችን ለዘላለም መኖር ሳይሆን የሚዘልቅ ነገርን ሰርቶ ማለፍ ነው" – Chuck Palahniuk

አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በአለም ላይ ከ100 ቢልየን ሕዝብ በላይ ኖሮ ሞቷል ተብሎ ይታመናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከ7 ቢልየን በላይ ሕዝብ በአለም ላይ ይኖራል፡፡ በቀን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከዚህ አለም ይሰናበታሉ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል እስካሁን ድረስ አለም በመልካም ስራቸው የሚያስታውሳቸው ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም፡፡ ከእነሱ ለሚበልጥ ነገር ኖረው የሞቱት ያኮሩናል፡፡ ሰዎች ከእነርሱ ለሚበልጥ ነገር ኖረው የመሞታቸው ምልክቱ እነሱ ካለፉ በኋላ የሚጸናን አሻራ ጥለው ማለፋቸው ነው፡፡ ከእነዚህ በተቃራኒ፣ እድሜአቸውን ለማይረባና ለሕብረተሰቡ ጥፋት ለሆነ ነገር ያሳለፉ ሰዎች ቁጥርም ጥቂት አይደለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ከእነሱና

ከማንነታቸው ላነሰ ነገር ኖረው ሞቱ ብንል አንሳሳትም፡፡ ሰው ከራሱ አልፎ ለሌላው ጥቅም ለመዋል የተፈጠረ ፍጡር ስለሆነ ከዚያ ላነሰና ለተለየ ነገር መኖር ከራስና ከማንነት በታች መኖር ማለት ነው፡፡

እኔና አንተም አንድ ቀን ቁጥራችን ከእነዚህ ከ100 ቢልየን ከሚበልጠው ሰዎች መካከል ይጨመርና ከኋላችን የሚመጣው ሕብረተሰብ እኛን በታሪክና በወረቀት ብቻ የሚያውቅበት ዘመን ይመጣል፡፡ የዛሬው ኑሮአችን ለወገናችን ያመጣው መልካም ተጽእኖ ትክክለኛ ስእል የሚታየው ያን ጊዜ ነው፡፡ ይህንን እውነታ በማሰብ የመልካም ተጽእኖ ሰው ለመሆን መነሳት እንዴት ያማረና ውብ የሆነ ነገር ነው፡፡ ለአንድነት፣ ለፍቅር፣ ለመቀባበልና ለመደጋገፍ፣ መሳሪያ ሆኖ መኖርና ማለፍ!

የሚከተሉትን እውነታዎች አሰላስላቸው፡-

ከራስ ወዳድነት ውጣ

ራስ ወዳድነት ማለት ከሌላው ሰው ጥቅም ይልቅ ለራስ ጥቅም ብቻ መኖር ማለት ነው፡፡ ራስ ወዳድ በዚህ አለም ላይ እሱ ብቻ እንደሚኖር የሚያስብ ሰው ነው፡፡ ሌላውን ጥሎ መነሳት፣ ሌላውን አከስሮ ትርፍ ማግኘት፣ ሌላውን አጥፍቶ መልማት፣ ... የራስ ወዳድ ሰው ዋና ዋና ምልክቶች ናቸው፡፡ ከዚህ "በሽታ" ነጻ የወጣ ሰው ከራሱ አልፎ ለሌላው ለማሰብ ራሱን የሰጠ ሰው ነው፡፡

ይህ ማለት ራሱን ይጥላል ማለት አይደለም፣ በተቃራኒው በእያንዳንዱ ስኬት ውስጥ ለሌላው የሚተርፍበትን መንገድ ያስባል ማለት ነው፡፡ ከራስ ወዳድነት ወጥተን ከሌላው ሰው አንጻር መኖር ስንጀምር ብቻ ሕይወት ሙሉ ትሆናለች፡፡

"ዘወትር ከሰዎች እየወሰደ እርሱ ግን ለሰዎች የማይሰጥ ሰው ይህንን በማድረግ ረጅም አመታት ሊቆይ ይችላል፣ ሕይወትን ግን አይኖራትም" – Unknown Source

ረጅም ዘመን መኖር አንድ ነገር ነው፣ የሕይወትን ጣእም ማጣጣምና ሕይወት የምትሰጠውን መልካም መዓዛ ማሽተት ደግሞ ከዚያ እጅግ የተለየ ጉዳይ ነው:: ለራሱ ብቻ የሚኖር ሰው በፍጹም የሕይወትን ትርጉም የማያውቅ ሰው ነው:: ቁም ነገሩ በሕይወታችን የምናስቆጥራቸው የቀናት ብዛት አይደለም፣ በቀኖቻችን ውስጥ ያለው የሕይወት ጣእም ጣፋጭነት እንጂ:: ራስ ወዳድ ሰው ይበላል፣ ሆኖም የሚቀጥለውን የሚበላ ነገር እያሰበ ስለሚበላ ምግቡን አጣጥሞ አይደሰትበትም:: ገንዘብ ይቆጥራል፣ ሆኖም የሚቀጥለውን ገንዘብ ከማን እጅ ፈልቅቆ እንደሚያወጣ እያሰበ ስለሚቆጥር የገንዘቡ ትርጉም ይሰወርበታል:: ያከማቻል፣ ነገር ግን ያከማቸውን ንብረት እንዳይነጠቅ ስለሚፈራ ስለእሱ ሲያስብ ሕይወት ታመልጠዋለች:: ይህንን ስንል ከራስ ወዳድነት ወጣ በማለት ከሌላው ሰው ጥቅም አንጻር መኖር የሚመች ጎዳና ነው ማለታችን አይደለም:: ምናልባት አንተ ለሌላው ስታስብ፣ በዙሪያህ ያለው ሰው ሁሉ ከራሱ አንጻር ሲሯሯጥ ስታየው፣ "ብቻዬን ምን አስለፋኝ" የሚል ስሜትን ሊሰጥህ ይችላል:: ለዚህ ስሜት እንዳትሸነፍ!

ተጽእኖ የሌለው ስራ እንደሌለህ አስብ

የምታደርጋቸው ማናቸውም አይነት ተግባሮች በሙሉ በሕብረተሰቡ ላይ ከፉ ወይም ደግሞ መልካም ተጽእኖ አላቸው:: ምርጫው የአንተ ነው:: ይህ ተጽእኖ ከቤትህ ይጀምራል:: ትዳር ካለህና ልጆች ከወለድክ በቤትህ የምታደርገው ነገር ሁሉ በባለቤትህም ሆነ በልጆችህ ላይ ተጽእኖ አለው:: አስተማሪ ከሆንክ፣ እነዚያ እንደ ነጭ ወረቀት ሊጻፍበት የተዘጋጀ አእምሮ ያላቸው ለጋ ልጆች በአንተ ተጽእኖ ስር ናቸው:: የአገር ወይም ደግሞ የአንድ ተቋም መሪ ከሆንክ የምታደርጋቸው እያንዳንዳቸው ነገሮችና ውሳኔዎችህ በብዙ ሕዝብ ላይ ተጽእኖ አላቸው:: በአጭሩ በሌላው ሰው ላይ ተጽእኖ የማያመጣ ተግባር የለህምና አስብበት::

"አንተ በወሰንከው ውሳኔ ሌሎችን ሰዎች መቅጣት የለብህም" – Dr. Laurence J. Peter

በሌላው ሰው ውሳኔና ግድ የለሽነት የተሞላበት ተግባር አንተ መጎዳት እንደማትፈልግ ሁሉ፣ በአንተም ውሳኔና ተግባር ሌላው ሰው መጎዳት እንደሌለበት ማሰብ ከባድ አይደለም:: አንዳንድ ተግባሮችህ ለአንተም ሆነ ለሌላው የማይጠቅሙ ናቸው:: ሌሎቹ ደግሞ አንተን ጠቅመው ሌላውን የሚጎዱ ናቸው:: ከዚህ ለየት ያሉት ደግሞ አንተን ጎድተው ሌላውን የሚጠቅሙ ናቸው:: ከእነዚህ አይነት ሁኔታዎች ለመጠበቅ ማመዛዘን አለብህ:: ከእነዚህ የላቀው ተግባር አንተም ሆንክ ወዳጆችህ፣ እንዲሁም በአካባቢህ ያሉ ሰዎች የሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው:: ይህንን አመለካከት በብቃት ስታዳብር ሚዛናዊ ሕይወትን መኖር ትጀምራለህ::

የሚቀጥለው ትውልድ ከአንተ እንዲሻል መንገድን ጥረግ

የሚቀጥለው ትውልድ ከአንተ የተሻለ ነገር እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለብህ:: የምትችለውን ያህል በልተህና መሰብሰብና ማካበት የምትችለውን ንብረት አካብተህ ለመኖር ከማሰብ መላቀቅም የስኬታማነትህ ምልክት ነው:: በእጅህ የገባውን ነገር በእጅህ ሲገባ ከነበረበት ሁኔታ በትንሽም ቢሆን አሻሽለህ ለሚቀጥለው ትውልድ ብታስተላልፍ ከብርህ የበዛ ይሆናል:: ይህ እንዲሆን ቆራጥ ውሳኔን ይጠይቃል:: የራሱን አገር አቆሽሾ ንጹህ አገር ፍለጋ ለመሄድ የሚነሳው ሰው ብዙ ነው:: አንተ ግን ለንጹህ ሃገር ወይም አካባቢ መስራት ትችላለህ:: የራሱን ሰው ንቆና ጎድቶ በፍጹም ሊከበርበት ወደማይችልበት አካባቢ መፍለስ የለመደ ሕብረተሰብ በአካባቢህ ትመለከት ይሆናል፣ አንተ ግን ለየት ያልክ ሰው መሆን ትችላለህ::

"በዚህ አለም ላይ የበሽታዎች ሁሉ በሽታ ለማንም ሰው ምንም አይነት መፍትሄ የማይሰጥ ሰው ሆኖ መኖር ነው" - Mother Teresa

Scanned with CamScanner

የአንድን ሰው ችግር ለማቃለል እንደተፈጠርክ አድርገህ ራስህን ማየት መጀመር አለብህ:: አንድን ነገር ለውጥ! አንድን መልካም ፈር ቅደድ! ለአንድ ሰው መፍትሄ ሁን! አንድ ሰው በብዙ ቢለፋ እንኳ በፍጹም ሊጨብጠውና ሊደርስበት የማይችለው ነገር አንተ ጋር ሊኖር ይችላል - ለዚህ ሰው ነገሮችን ልታቀልለትና መንገድ ልትከፍትለት ትችላለህ:: በዘመንህ ያሉትን ለራሳቸው ብቻ ለመኖር የወሰኑትን ሰዎች የሚያሳፍርና ከአንተ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ደግሞ ፈር የሚቀድድ መንገድ ፍጠር:: ይቻላል!!!

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የዘላቂነት አመለካከት ምክሮች:-

1. ከራስ ወዳድነት ውጣ
2. ተጽእኖ የሌለው ስራ እንደሌለህ አስብ
3. የሚቀጥለው ትውልድ ከአንተ እንዲሻል መንገድን ጥረግ

ሰዎች ከአነርሱ ለሚበልጥ ነገር ኖረው የመሞታቸው ምልከቱ እነሱ ካለፉ በኋላ የሚጸናን አሻራ ጥለው ማለፋቸው ነው::

10

እንዳያይ ሳይሆን እንዳያተኩር

የትኩረት ቁልፍ

አንዳንድ ሰዎች የሚያስገርምን ብቃት፣ ሌላው ያላገኘውን ታላቅ እድልና የተመቻቸ ሁኔታ ይዘው ሳሉ ሲባክኑና አንድም ነገር ሳያከናውኑ ሲያልፉ የሚታየው ለምንድን ነው? የተበታተነና ትኩረቱን ያጣ ማንነት ስላላቸው ነው:: የእውቀት ጥልቀት፣ የዲግሪ ብዛት፣ የሃብት መትረፍረፍ፣ የጉልበት ብርታት፣ የዝና ስፋት፣ የውበት ተደናቂነትና እንዲሁም አለ የተባለ ተቀባይነት ከትኩረት ውጪ ባዶ ነው:: የተበታተነና በአንድ ነገር ላይ ያላተኮረ አመለካከት የባከነ ማንነት ነው:: ሰው ሁሉም እያለው ምንም እንደሌለው ባከኖ ኖሮ የሚያልፈው ትኩረትን ሲያጣ ነው:: የተሰበሰበና ያተኮረ ማንነት አንዱ የስኬት ቁልፍ ነው::

የእንስሳ አሰልጣኙ ወደ አንበሳው ሲቀርብ ለማንኛውም ለመከላከያ የሚሆንን ነገር መያዙ ጥርጥር የለውም:: ድንገት ይህ የዱር እንስሳ አውሬነቱ ቢያነሳሳውና ለማጥቃት ቢነሳ ራሴን አድንበታለሁ የሚለውን መሳሪያ መያዙ ነፍስ አድን ቢሆንም፣ ለአሰልጣኙ ግን ከዚያ ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነገር አለ:: ይህ ሰው ወደ አደገኛው አንበሳው ሲጠጋ በእጁ የሚይዘው ዋነኛ ነገር አራት እግር ያለው ወንበር ነው:: ይህ ሰው ወደ አንበሳው በቀስታ ሲቀርብና በእጁ የያዘውን የወንበር እግሮች በአንበሳው ፊት ሲደነቅረው

Scanned with CamScanner

የአንድን ሰው ችግር ለማቃለል እንደተፈጠርክ አድርገህ ራስህን ማየት መጀመር አለብህ:: አንድን ነገር ለውጥ! አንድን መልካም ፈር ቅደድ! ለአንድ ሰው መፍትሄ ሁን! አንድ ሰው በብዙ ቢለፋ እንኳ በፍጹም ሊጨብጠውና ሊደርስበት የማይችለው ነገር አንተ ጋር ሊኖር ይችላል - ለዚህ ሰው ነገሮችን ልታቀልለትና መንገድ ልትከፍትለት ትችላለህ:: በዘመንህ ያሉትን ለራሳቸው ብቻ ለመኖር የወሰኑትን ሰዎች የሚያሳፍርና ከአንተ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ደግሞ ፈር የሚቀድድ መንገድ ፍጠር:: ይቻላል!!!

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የዘላቂነት አመለካከት ምክሮች:-

1. ከራስ ወዳድነት ውጣ
2. ተጽእኖ የሌለው ስራ እንደሌለህ አስብ
3. የሚቀጥለው ትውልድ ከአንተ እንዲሻል መንገድን ጥረግ

ሰዎች ከአነርሱ ለሚበልጥ ነገር ኖረው የመሞታቸው ምልክቱ እነሱ ካለፉ በኋላ የሚጸናን አሻራ ጥለው ማለፋቸው ነው::

10

እንዳያይ ሳይሆን እንዳያተኩር

የትኩረት ቁልፍ

እንዳንድ ሰዎች የሚያስገርምን ብቃት፣ ሌላው ያላገኘውን ታላቅ እድልና የተመቻቸ ሁኔታ ይዘው ሳሉ ሲባክኑና አንድም ነገር ሳያከናውኑ ሲያልፉ የሚታየው ለምንድን ነው? የተበታተነና ትኩረቱን ያጣ ማንነት ስላላቸው ነው:: የእውቀት ጥልቀት፣ የዲግሪ ብዛት፣ የሃብት መትረፍረፍ፣ የጉልበት ብርታት፣ የዝና ስፋት፣ የውበት ተደናቂነትና እንዲሁም አለ የተባለ ተቀባይነት ከትኩረት ውጪ ባዶ ነው:: የተበታተነና በአንድ ነገር ላይ ያላተኮረ አመለካከት የባከነ ማንነት ነው:: ሰው ሁሉም እያለው ምንም እንደሌለው ባክኖ ኖሮ የሚያልፈው ትኩረትን ሲያጣ ነው:: የተሰበሰበና ያተኮረ ማንነት አንዱ የስኬት ቁልፍ ነው::

የእንስሳ አሰልጣኙ ወደ አንበሳው ሲቀርብ ለማንኛውም ለመከላከያ የሚሆነን ነገር መያዙ ጥርጥር የለውም:: ድንገት ይህ የዱር እንስሳ አውሬነቱ ቢያንሳሳውና ለማጥቃት ቢነሳ ራሴን እድንበታለሁ የሚለውን መሳሪያ መያዙ ነፍስ አድን ቢሆንም፣ ለአሰልጣኙ ግን ከዚያ ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነገር አለ:: ይህ ሰው ወደ አደገኛው አንበሳው ሲጠጋ በእጁ የሚይዘው ዋነኛ ነገር አራት እግር ያለው ወንበር ነው:: ይህ ሰው ወደ አንበሳው በቀስታ ሲቀርብና በእጁ የያዘውን የወንበር እግሮች በአንበሳው ፊት ሲደነቅረው

የአንበሳው አይኖች ከአንዱ ወደሌላ ይንከራተታል:: የአንበሳው አይንና ሃሳብ ከአንዱ የወንበር እግር ወደሌላኛው ሲንከራተት ትኩረቱ ይሰረቃል:: ዋናው ሊተኩርበት የሚገባውና ለምግብነትም ሊያገለግል የሚችለው ሰውየው ሆኖ ሳለ፣ ከተፈጠረው ትኩረት የማሳጣት ሁኔታ የተነሳ ሰውየው ከመታየት ወደ አለመታየት ይሰወራል:: አሰልጣኙ ወንበሩን በእጁ የመያዙ ዋነኛ ዓላማ አንበሳው እንዳያይ ሳይሆን እንዳያተኩር ነው::

"ብዙ ነገሮችን የማከናወኛው አጭሩ መንገድ በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር ማድረግ ነው" – Mozart

በአንድ ጊዜ ከአንድ ነገር በላይ ለመጨበጥ የሚሯሯጥ ሰው - አሳዛኝ ሰው! ከአንዱ አላማ ወደ ሌላኛው፣ ከአንዱ የፍቅር ሕይወት ወደ ሌላኛው፣ ከአንዱ የትምህርት ሁኔታ ወደ ሌላኛው፣ ከአንዱ ስራ ወደ ሌላኛው ... ማለቂያ የሌለው ልፋት::

የተበታተነ አመለካከት ውጤት የተበታተነ ሕይወት - ሂሳቡ ይህ ነው! በዘመናት ሁሉ የተሳካላቸው ሰዎች የስኬታቸው አንዱ ቁልፍ ይህ ነው - ትኩረት! እነዚህ ሰዎች ስለተሳካላቸው አይደለም ትኩረትን ያገኙት፣ ትኩረት ስለነበራቸው ነው ወደ ስኬት የዘለቁት::

በእኔና በአንተም ሕይወት እውነታው ከዚህ የተለየ አይደለም:: ስኬት የሞላው ሕይወት ለመኖር ካስፈለገ በዋነኛው ነገር ላይ ማተኮር የግድ ነው:: ይህ ከሆነበት ምክንያት አንዱና ቀደምተኛው አንተነትህ አንድ የመሆኑ ጉዳይ ነው - አንድ ነህ! ለመሆንም የተፈጠርከው አንድን ማንነትን ነው:: ይህ ማንነት ደግሞ በአንድ ነገር ላይ ሲያተኩር ይቀናዋል:: ሌላው እውነት፣ ከአንድ ነገር ላይ ሃሳብህን አንስተህ ሌላ ነገር ላይ ስታተኩር ቀድሞ የጀመርከው ነገር ባለበት የመቆሙ ወይም ለአደጋ የመጋለጡ እውነት ነው:: ይህን እውነት በሌላ ግልጽ በሆነ መልኩ ለማሳየት ልሞክር:: በከተማችን መኪና እያሽከረከሩ ስልክ ማነጋገር የመከልከሉ ምክንያት ምን ይመስልሃል? ሰዎች

ትኩረታቸውን ከአንድ ነገር በላይ ላይ የማድረግ ብቃታቸው እጅግ አናሳ በመሆኑ ነው:: አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙን የሞባይል ስልክ እየተጠቀሙ ማሽከርከር ለአደጋ የመጋለጥ ሁኔታን 30 በመቶ እንደሚጨምረው ነው:: ተመሳሳይ ጥናት እንደሚጠቁመን፣ ገመድ አልባ ስልክ እየተጠቀሙ መኪና ማሽከርከር በመንዳትና በመኪናው ላይ ልናውለው የሚገባንን 37 በመቶውን ትኩረት ይሰርቅብናል::

ለትኩረት የሚረዱ እውነታዎች፡-

በሚሳካልህ ነገር ላይ አተኩር

ብዙ ሰዎች የሚሳካላቸው ነገር ላይ ከማተኮር ይልቅ የማይሳካላቸው ጉዳይ ላይ ማተኮር ይመርጣሉ:: መሆን የሚገባው ግን የማይሳካልንን ነገር ትተን በማድረግ የሚሳካልን ላይ መገንባት ነው:: ከልጅነታችን ጀምሮ ሰዎች ያልተሳካልንና ያቃተን ነገር ላይ ነው ሃሳብ ሲሰጡን ያደግነው:: ቤተሰቦቻችን ጥሩ ውጤታችንን አይተው ከሚያመሰግኑን ይልቅ መጥፎ ውጤት ሲመጣ የሚቆጡን ይበዛል:: ይህ ሁኔታ ትኩረታችን ያልተሳካው፣ የሚያታግለንና አልሆን ያለን ላይ እንዲሆን በውስጣችን ዝንባሌን ፈጥሮአል:: ይህ ዝንባሌ መወገድ አለበት:: ወፍ የሚቀናት በአየር ላይ ስትበር ነው፣ አሳ የሚሆንለት በውኃ ውስጥ ሲዋኝ ነው፣ ፈረስ የሚሳካለት በምድር ላይ ሲገሰግስ ነው::

እነዚህ ፍጥረቶች በአንድም ሆነ በሌላ ጊዜ ያኛውን ሞክረውት ቢያውቁም ብዙ ጊዜአቸውን የሚያጠፉት ግን የሚችሉበትን ደጋግሞ በማድረግ ነው:: የአንተም ሁኔታ ከዚህ አይለይም:: የማትችለውን አልፎ አልፎ ሞክር፣ ትኩረትህን ግን በሚቀናህና ውስጥህን በሚያነሳሳው ላይ መጣል አለብህ::

"በዚህ አለም ላይ የአንተን ችሎታ ሊጠቀም የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነው፤ እሱም አንተው ነህ" - Zig Ziglar

እንደ ጋር ያለውን ብቃት ለማጠናከርና ሊያሳድገው የሚችለው አንተው ብቻ ነው። ሌላው ሰው በዚያው ቅጽበት የአንተ ብቃትና ማንነት ሊያዳብር አይችልም። እንዲሁ ሌላኛው ሰው በሰራው ስራ ተጠቅሞ ውጤቱን ማሳደግ እንደሚችል ሁሉ አንተም የራስህን ብቃት አንተው ነህ ማሳደግ ያለብህ። ብቃትህን በሚገባ በሙያ ላይ እንድታተኩር ካስፈለገ ደግሞ ራስህን ማወቅ ዋናው ነው። አንተ ብቃትህን ከአንተ በበለጠ ሁኔታ ሊያውቀው የሚችል ሌላ ሰው የለም። ይሄንን ማንነትህን በሚገባ ወደማወቅ ለመምጣት የሚያስችልህን ከሚያደርስልህ ስራ ላይ ትኩረትህ ግን ያስፈልጋል። ይህ ሁኔታ ትንሽ ጊዜ ሊፈጅ የሚችል ቢሆንም እንኳ ብዙ ሳይቆይ ትርጉምና ቢሆን የሚያደርግህን ነገር ለማከናወን ራስህን ታገኘዋለህ።

በየቀኑ በሚሳካልህ አንጻር ገንባ

በየእለቱ የምታስበው፣ የምትተገብረው፣ የምታገኘውም ሆነ የምታቅደው ነገር ከሚሳካልህና ከአላማህ አንጻር ሊሆን ይገባዋል። አስተማሪ ከሆንክ በምታስተምረው ነገር ዙሪያ በየቀኑ እውቀትን መሰብሰብ አለብህ። ምናልባት ወደፊት ማግኘት የምትፈልገውና በልብህ እንደ እሳት የሚንበለበል ነገር ካለ፣ ትኩረትህን በዚያ ዙሪያ እንድታደርግ ለስኬት ቅርብ የሚያደርግህ ነገር የለም። ለምሳሌ፣ ለማወቅ በምትጓጓለት ነገር ላይ በቀን አንድ ምእራፍ ማንበብ ብትጀምር፣ በአንድ አመት ውስጥ የሚኖርህ እድገት መገመት አያስቸግርም። ይህ አይነቱ ትኩረት ነው ከአማካኝ ሕዝብ ቀድሞ እንድትሄድ የሚያደርግህ።

“ችሎታ ማድረግ የምትችለውን ብቃትህን ያሳያል። መነሳሳት ብቃትህን በተግባር የማዋልህን ሁኔታ ይወስናል። ዝንባሌ ግን የተግባርህን ጥራት ይወስናል” – Lou Holtz

ችሎታ ብቻውን ምንም እንደማያደርግልህ እወቅ። ችሎታ አንድን ነገር የማድረግ ብቃት እንዳለህ ብቻ አመልካች ነው። አስገራሚ ችሎታ ያላቸው፣ ነገር ግን ለምንም ጥቅም

የሚያደርጉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ አትዘንጋ። በችሎታህ ላይ መነሳሳትና ጽኑ ዝንባሌ ካልጨመርክበት ይቀራል። ያለህን መነሳሳት በማዳበርና በየቀኑ አንድን ነገር በማድረግ ከወራትና ከአመታት በኋላ የተጠራቀመውና የተገነባ ነገር ማግኘት ትችላለህ። መነሳሳት ችሎታህን በተግባር ላይ እንድታውለው ሲረዳህ ዝንባሌህ ግን የምታደርገውን ነገር በምን አይነት "መንፈስ" እንደምታደርገው ይወስናል። ይህ እጅግ አስፈላጊ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ምንም አይነት ችሎታ ቢኖርህ ለመተግበርም ያህል መነሳሳት ቢኖርህ እንኳ ዝንባሌህ የደከመ፣ የመጥፎና በእይታ የተሞላ ከሆነ መጨረሻው አያምርም። ስለዚህ አዎንታዊ ዝንባሌ ይኑርህ።

ከዓላማህ በፍጹም አትላቀቅ

በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡና እቅዶቻቸውን የሚተዉ ሰው አትሁን። ከምትሰራበት አንጻር እንጂ "ከሚገጥመው" አንጻር ለመገምገም አትሞክር። የአንተ የወደፊት ጉዞ ከምትሰራው ጋር እንጂ በሰዎች ላይ ከሚገጥመው የጊዜው ገበያ ጋር አይደለም። ባለህበት በመገኘት በምትሰራበት ነገር "ጊዜያዊ" በሚባለው ነገር ውስጥ እንኳ ላይቋረጥ እንድትቀጥል ዝንባሌህን የሚያጠናክሩ ከፍተኛ አለ። የገበያ አያያዝ ብልሃት በውስጥህ አይቀር፣ ጉዞ ያበዛል ለዘላለም ብቻ ነገሮች ለመሆን መነሳት መሳካት ነው። በምትሰራበት ገበያውን በቅጡ መያዝ ለማይችሉ ነጋዴዎች የገበያ አያያዙን መፍትሄ ልታቀርብ ትችላለህ። ይህ አሰራር በጊዜው ያለህ የትርፍ ሽያጭ አንዳንዴ ሲሆን የሚያስገኝ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣ ለጊዜው ያለህን የትርፍ ውጥረት ለማስተንፈስ ከአንተነትህ ጋር የሚጋፋ ነገር ብታደርግም፣ ውስጥህ ግን በፍጹም ከዋናው አላማህ መለያየት የለበትም።

“ታላላቅ ስራዎች የሚከናወኑት በታላቅ ጉልበት ሳይሆን ሳያቋርጡ በመስራት ነው” –

Samuel Johnson

Scanned with CamScanner

ውጤት የምታገኘው በአንድ ጊዜ ባንጠባጠብከው የላብ ብዛት አይደለም፤ ካለማቋረጥ ውጤት እስከምታገኝ ድረስ በተገበርከው ተግባር እንጂ:: አንድን ነገር ለማግኘት መመኘትም ስኬት አይሰጥህም:: በቅድሚያ በልብህ የሞላውንና ያመንከበትን ነገር ለመጀመር የቆረጥክ የመሆንህ ጉዳይ አስፈላጊ ነው:: በመቀጠልም ያንን የጀመርከውን ነገር እስከትጨርስ ድረስ በተግባርህ መጽናት አለብህ:: ከዚያም የጀመርከውን ነገር ላለመጨረስ ምንም ምክንያት አትስጥ:: የስኬት ነገር የሚወሰነው የሕይወት ተራራን በምን ያህል ጉልበት እንደገፋህ ብቻ አይደለም ለምን ያህል ጊዜ በጽንአት እንደገፋህ ነው::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የትኩረት ቁልፎች:-

1. በሚሳካልህ ነገር ላይ አተኩር
2. በየቀኑ በሚሳካልህ አንጻር ገንባ
3. ከአላማህ በፍጹም አትላቀቅ

የተበታተነ አመለካከት ውጤት የተበታተነ ሕይወት - ሂሳቡ ይህ ነው!

11

እንድ ቀን በጨረቃ ላይ እራመዳለሁ

የራእይ ቁልፍ

በሕይወታችን የሚቻለውንና የማይቻለውን የሚወስነው ማን ነው? ገደባችንስ ምንድን ነው? ካለንበት ተነስተን መድረስ ወደምንፈልግበት ቦታ ለመድረስ የሚያስፈልገን ዋነኛ እውነታ ምንድን ነው? አይታ! የአንድ ሰው አይነህሊና ሲበራ የማይቻለው ወደመቻል ይመጣል - በድንገትም ሆነ በሂደት! ከዚህ በፊት ያልተቻለው ነገር ያልተሞከረው ነገር ነው፤ ያልተሞከረው ነገር ደግሞ በአይነ-ህሊናና በይቻላል መንፈስ ለማየት ያልደፈርነው ነገር ነው:: በማየት፣ በማመን፣ በመንቀሳቀስና ሲወድቁ ተነስቶ በመቀጠል የማይቻል ይቻላል::

ጄምስ አርዊን (James B. Irwin) እንደማንኛውም ልጅ በአማካኝ ቤት ውስጥ ያደገ ሰው ነው:: በውስጡ ግን ያልተለመደ አይታ የነበረው ልጅ ነበር:: በአንድ ምሽት ጄምስ ራቱን ከበላ በኋላ ሲጫወት ሳለ እናቱ፣ ሰዓቷን ካየች በኋላ፣ "መሽቷልና ወደ መኝታህ መሄድ አለብህ፣ እኔ ስራዬን ስጨርስ እመጣለሁ" ብላ ወደ ክፍሉ ላከችው:: በዚያ ጨረቃዋ ደምቃ በምትታይበት ብሩህ ምሽት ጄምስ ወደክፍሉ የሚወስደውን ደረጃ ከወጣ በኋላ ክፍሉ ውስጥ ተቀመጠ:: እናቱ ከአንድ ሰዓት በኋላ ልታየው ስትሄድ ጄምስ በመስኮቱ አጠገብ ተቀምጦ ብሩኋን ጨረቃ ትኩር ብሎ ሲያይ

አገኘችው:: በመገረም፣ “ምን እያደረግህ ነው” በማለት ጠየቀችው:: “ጨረቃዋን እያየሁ ነው” አላት:: “የመኝታህ ሰዓት አልፏል፣ መተኛት ነበረብህ እኮ” አለችው:: በማጉረምረም ወደ መኝታው እየሄደ እንዲህ አላት፣ “አንድ ቀን በጨረቃ ላይ እራመዳለሁ”:: አይሮፕላን በበረራ ስልጠና የተመረቀው ጄምስ፣ በአንድ ወቅት በልምምድ አይሮፕላኑ ላይ ከደረሰው የመከስከስ አደጋ ተርፏል:: ከዚያም በተጨማሪ በተለያዩ የሕይወት ውጣ ውረዶች እንዳለፈ ይነገራል:: ጄምስ አርዊን ያንን ራእይ የተሞላበትን ሃሳብ ለእናቱ ከተናገረ ከ32 ዓመታት በኋላ ጨረቃ ላይ እግራቸው ከረገጡት ሰዎች መካከል ራሱን አገኘው:: የእይታ ጉልበት!!!

“የወደፊቱን የሚወርሱ ሰዎች ሁኔታዎች እውን ከመሆናቸው በፊት እንደሚቻሉ አስቀድመው የሚያዩ ሰዎች ናቸው” – John Sculley

ሰው አይነ-ህሊናው ሳያይ እንዴት ወደ አላማው ይራመዳል? ሳይራመድስ እንዴት ወደ አንድ ደረጃ ይደርሳል? የብዙ ሰዎች ሕይወት የመላ-ምት ሕይወት ነው:: የመጣው ነገር ሁሉ በቀላሉ ከአንዱ ሃሳብ ወደሌላኛው ይወስዳቸዋል:: በር ስለተከፈተ ብቻ ይገባሉ፣ የሚበላ ስለተገኘ ብቻ ይበላሉ፣ ሰው ስለተገኘ ብቻ ጓደኝነት ውስጥ ዘልቀው ይገባሉ::

የሚወስኑት ውሳኔና የሚከተሉት ጎዳና ከዋና ራእያቸው ጋር አብሮ የመሄዱና የመመጣጠኑ ነገር ትዝም አይላቸው - ለዚያውም ራእይ ካላቸው ነው:: ስለዚህ በአንዱ የገነቡትን በሌላኛው ያፈርሱታል:: ለብዙ አመታት በመከተል ጊዜአቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ያፈሰሱለትን ነገር በጥቂት ጊዜአዊ እይታ ትተውት ይሄዳሉ:: ስኬታማ ሰዎች ግን ከዚህ ይለያሉ:: ስኬታማ ሰዎች የራእይ ሰዎች ናቸው:: የስኬታማ ሰዎች ራእያቸው የመነጨው ከስኬታማነታቸው አይደለም፣ ባለራእይ ከመሆናቸው የተነሳ ነው ስኬታማነት የተከተላቸው:: እነዚህ ሰዎች የውስጣቸው እይታ ሃይለኛ ነው:: በአይነ-ህሊናቸው ያያሉ፣ ያልማሉ፣ ወደ ራእያቸውም ይገሰግሳሉ:: ሶስት ወሳኝ ጥያቄዎች:-

ራእይህ ምንድን ነው?

ውስጥህ ምንን ያያል? በሚቀጥሉት ከአምስት እስከ አስር አመታት ውስጥ ለማድረግ ወይም ለመሆን የምትፈልገውን ነገር ቁልጭ ባለ መልኩ በአንዲት ገጽ ውስጥ ማስፈር ካልቻልክ ምናልባት ካለራእይ የምትንከራተት ሰው ነህ ብዬ እሰጋለሁ:: ማን ነህ? ምን መሆን ነው የምትፈልገው? ምንስ ማከናወን ትፈልጋለህ? ውስጥህን የሚፈታውና የሚያነሳሳው ነገር ምንድን ነው? ሕይወትህን እስከመሰዋት ድረስ ራስህን የምትሰጥለት እውነት አለ? እነዚህ የራእይ ጥያቄዎች ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው፣ ምክንያቱም በሕይወትህ የምትመኛቸውን ነገሮች ወደመሆን የምታመጣበት ብቸኛ መንገድ ራእይ ስለሆነ ነው:: ይህ ራእይ ደግሞ ግልጽና ግራ የማያጋባ ሊሆን ይገባዋል::

“ራእይ ማለት ለሌሎች የማይታየውን ነገር ማየት ማለት ነው” - Jonathan Swift

ራእይን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ እኛ የምናየውን ነገር ሌሎች ለማየት አለመቻላቸው ነው:: አንዳንድ ጊዜ እኛ ያየነውን ነገርና ለማድረግ በጽኑ የፈለግነውን ነገር ያዩልናል የምንላቸው የቅርብ ወዳጆችን እንኳ ላያዩት ይችላሉ:: ሁኔታው ደግሞ ልብን ሊያዝል ይችላል::

ምክንያቱም እኛ ያየነውን ያላዩ ሰዎች የምንጠብቀውን ድጋፍ ሊሰጡን ስለማይችሉ ነው:: ስለዚህም ልብን ከመራራነትና አልደገፉንም ብለን ባሰብናቸው ሰዎች ላይ ቂም ከመያዝ ልንጠብቅ የግድ ነው:: ከሰዎች ያጣነው ተቀባይነትና ድጋፍ በራእያችን ላይ ምንም ችግር ሊያመጣ አይችል:: ለዚህ የመገፋት ስሜት የምንሰጠው ምላሽ ግን ከጎዳናችን ያወጣናል:: ለማከናወን ውስጥህ ያየውን ነገር ሰዎች እንደ እንግዳ ነገር ሲቆጥሩብህ አትረበሽ::

Scanned with CamScanner

በራእይህ ታምንበታለህ?

በራእይህ ካመንክበት ሌላው ሰው ሳያምንበት እዚያ ራእይ ላይ ልትደርስ ትችላለህ፤ በራስህ ራእይ አንተው ካላመንክበት ግን በፍጹም ልትደርስበት አትችልም:: ይህ እንዲሆን ራእይህ በሌላው ሰው ብርታት፣ እውቀትና ድጋፍ ላይ ያልተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል:: ራእይህ እውን የመሆኑንና ያለመሆኑን ጉዳይ የሚወስነው ብቸኛ ሰው አንተው ነህ:: ይህ የሆነበት ምክንያት ራእዩ የተፈጠረው በአንተው "የእይታ ማህጸን" ውስጥ በመሆኑ ነው:: ይህንን የራእይ ጽንስ ሊሸከመው፣ ሊመግበውና፣ ሊያሳድገው የሚችለው የአንተው "የራእይ ማህጸን" ነው:: ስለዚህም፣ በራእይህ ሙሉ በሙሉ ልታምንበትና ከልብህ ልትገነባው ያስፈልጋል::

"ብዙ ሰዎች ሌሎች ሰዎች ናቸው:: ሃሳባቸው የሌላ ሰው አስተያየትና ሃሳብ ነው፣ ሕይወታቸው ቅጂ ነው፣ የሚያንቀሳቅሳቸውም የሰው አባባል ነው" – Oscar Wilde

በተለያየ መልኩ ሰዎች ተጽእኖ ያሳድሩብሃል፣ አንዳንዶቹ ክፉ ሌሎቹ ደግሞ መልካም:: ከክፉው ተጽእኖ ራስህን ማላቀቅ እንዳለብህ የሚያነጋግር ጉዳይ አይደለም:: በተቃራኒው መልካም ተጽእኖ የሚያሳድሩብህን ሰዎች መቅረብና ያንን እንዲያደርጉ መንገዱን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው:: ሆኖም ማንነትህን በሙተው የእነሱን ማንነት ለመኖር ወደመሞከር እንዳታቀና መጠንቀቅ አለብህ:: ምንም አሰብከ ምንም፣ ሃሳቡ የአንተው መሆኑን አርግጠኛ ሁን:: ምንም ተሰማህ ምንም፣ ስሜቱ የአንተው ስሜት መሆኑን አርግጠኛ ሁን:: በራእይህ ሙሉ በሙሉ ለማመንና ለመከተል በቅድሚያ ራስህን ሆነህ መገኘት አስፈላጊ ነው::

ራእይህን በጋለ ስሜት ትከታተለዋለህ?

መኪናዎች ከአንድ ቦታ ተነስተው ወደ ሌላኛው እንዲደርሱ መንቀሳቀስ አለባቸው:: መንቀሳቀስ ደግሞ ነዳጅ ያስፈልጋቸዋል:: የራእይም ነገር እንዲሁ ነው:: ራእይህን ለመንቀሳቀስ ደግሞ ነዳጅ ያስፈልጋቸዋል:: ...

ትክክለኛ ባለራእይ ከእርሱ ለበለጠ ነገር ለመኖር የተነሳ ሰው እንደሆነ አትዘንጋ:: ከአንተ ለበለጠ ነገር መኖር ሕይወትህን እጅግ ባቋጭ ያደርገዋል:: ከአንተ የበለጠ ነገር ማለት ከገንዘብህ፣ ከእውቀትህና ከአስተዳደግህ የበለጠና የላቀ ነገር ማለት ነው:: ይህ ነገር ታላቅ ትልበትን ይጠይቃል::

"ምኑን የሚያንቀሳቅሰው ምንድን ነው? ጽኑ ፍላጎት፣ ጽኑ ፍላጎት፣ ጽኑ ፍላጎት!" – Stanley Kunitz

"ሰው ካለምግብ ለብዙ ቀናት መቆየት ይችላል፣ ካለውኃ ደግሞ ለጥቂት ቀናት መኖር ይችላል፣ ከተስፋ ውጪ ግን ለአንድ ሰከንድ መኖር አይችልም" ይባላል:: ተስፋ ማለት ምንድን ነው? ተስፋ ማለት ነገ እንደርስበታለን ወይም እንጨብጠዋለን ብለን ያመንነው ራእይ ወይም ሕልም አይደለም? ይህንን ሕልም ሊያንቀሳቅሰው የሚችለው ብቸኛ ነዳጅ የጽኑ ፍላጎት ነዳጅ ነው::

ጽኑ ፍላጎትና የጋለ ስሜት ተራራውን አልፈህ እንድትሄድ የማድረግ ኃይል አለው:: ከተራራው ባሻገር ያለውን ራእይህን ለመጨበጥ ያለህ ፍላጎት ሲጸናብህ፣ ተራራው

Scanned with CamScanner

መናድ ከተቻለ ትንደዋለህ፤ ካልተቻለ ትቦረቡረዋለህ፤ ያም ካልተቻለ በ[illegible] ተሻግረህም ቢሆን ታልፋለህ፤ ይህኛውም ካልተቻለ በዙሪያው አልፈህ ወደ ራእይህ ዘልቀህ ትሄዳለህ:: ይህ የሚቻለው የጽኑ ፍላጎት ነዳጅ በውስጥህ ሙሉ ሲሆን ነው:: የእንቅፋቱ ብዛት ብዙዎችን ባደከመበት በዚህ ክፍለ ዘመን፣ በጽኑ ያልተከታተልከው ነገር ላይ በፍጹም እንደማትደርስበት ሳላስታውስህ አላልፍም::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ራእይን የማወቂያ ጥያቄዎች:-

1. ራእይህ ምንድን ነው?
2. በራእይህ ታምንበታለህ?
3. ራእይህን በጋለ ስሜት ትከታተለዋለህ?

የስኬታማ ሰዎች ራእያቸው የመነጨው ከስኬታማነታቸው አይደለም፣ ባለ ራእይ ከመሆናቸው የተነሳ ነው ስኬታማነት የተከተላቸው::

12

ቴርሞሜትር ነህ ወይስ ቴርሞስታት?

ነገሮችን ወደ መኖር የማምጣት ቁልፍ

በሕይወትህ የሚመጣውን ነገር ዝም ብለህ አስተናጋጅ ነህ ወይስ ሁኔታዎችን ለመለወጥ የምትንቀሳቀስ የለውጥ ሰው? አንዳንድ ሰዎች ሁኔታዎች የእነሱን አቅጣጫ እንዲወስኑ ይፈቅዳሉ፣ ሌሎች ግን ሁኔታዎችን ይቆጣጠራሉ እንጂ በቀላሉ በሁኔታዎች ቁጥጥር ስር አይውሉም:: ምርጫችን ሁለት ነው፣ የመጣውን ነገር ዝም ብሎ ማስተናገድ ወይም የመጣውን ነገር ከአላማችን አንጻር ለመቃኘትና ለመለወጥ መነሳት:: ምርጫችን ሁለት ነው፣ የእለቱን የአየር ጸባይ ማወጅና ማጋነን ወይም የአየሩን ሁኔታ ለቆምንለት ዓላማ እንዲመጥን አድርጎ መቆጣጠር:: ምርጫችን ሁለት ነው፣ ክስተቶችን ቁጭ ብሎ በመጠበቅ ወዲህና ወዲያ መንገላታት ወይም ነገሮችን ወደመሆን ለማምጣት መስራት::

የእለቱን የአየር ጸባይ የምናስተናግድባቸው ሁለት አስፈላጊ መሳሪያዎች አሉን:: አንደኛው "ቴርሞሜትር" (Thermometer) ሲሆን ሌላው ደግሞ "ቴርሞስታት" (Thermostat) ነው:: ቴርሞሜትር የሚለው ስም ከሁለት የግሪክ ቃላት ጥምረት የመጣ ነው:: "ቴርሞ" (thermo) ማለት "ሙቀት" ማለት ሲሆን፣ "ሜትር"(meter) ማለት ደግሞ "መለካት" ማለት ነው:: ከትርጉሙም፣ ሙቀትን መለካት የሚለውን ሃሳብ እናገኛለን:: ቴርሞሜትር የእለቱን የአየር ጸባይ ይለካና ይነግረናል:: ብርዱን ብርድ፣

Scanned with CamScanner

ሙቀቱን ሙቀት ይለናል፣ መጠኑንም ቁልጭ አድርጎ ያስታውቀናል:: በተቃራኒው “ቴርሞስታት” የሚለውም ስያሜ ከሁለት የግሪክ ቃላት ጥምረት የመጣ ነው:: “ቴርሞስ” (thermos) ማለት “ሙቀት” ማለት ሲሆን፣ “ስታቶስ”(statos) የሚለው ቃል ደግሞ “መጠን” ወይም “ደረጃ” የሚለውን ሃሳብ ያቀፈ ነው:: ቴርሞስታት እኛ በሰጠነው የአየር ሙቀት መጠን የእለቱን የአየር ጸባይ ላለንበት ስፍራና ሁኔታ በሚመች መልኩ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል:: የሙቀቱን እውነታ ዝም ብለን እንድንቀበለው ሳይሆን በሚመጥነን መልኩ እንድንቆጣጠረው ይረዳናል::

“ሁኔታዎችን ጊዜ ይቀይራቸዋልና ጠብቅ የሚል የተለመደ አባባል አለ፣ ነገር ግን ሁኔታዎችን አንተው ራስህ ነህ መቀየር ያለብህ” – Andy Warhol

ሰው ተፈጥሮ የሚሰጠውን ሁኔታ ዝም ብሎ ቢቀበል በዚህ ምድር ላይ መኖር አይችልም:: የቅዝቃዜው መጠን ደምን እስከማርጋት በሚደርስበት አካባቢ ሰው የሚኖረው እንዴት ነው? የሙቀቱ ግለት ለሰከንድ እፍታ በማይሰጥበት አካባቢስ ሰው እንዴት መኖርን ቻለው?

አየሩን በመቆጣጠር! ሰው በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ መኖር የሚያስችል ብቃት አለው - የሚያደርገውን ካወቀ! በሕይወትህ የሚመጡትን ሁኔታዎች ቁጭ ብለህ የምትጠብቅና የመጣው ነገር ሁሉ ወዲህና ወዲያ እንዲያንገላታህ የምትፈቅድ ሰው ከሆንክ አንደኛህን የስኬትን ነገር ለጊዜው ብትተወው ይሻልሃል:: ስኬታማ የሆኑ ሰዎች ሁኔታዎችን ለእነርሱ አላማ ለማስገዛት ጠንክረው የሚሰሩ ሰዎች ናቸው:: ሁኔታዎች እነሱን እንዲገዟቸው በፍጹም አይፈቅዱም:: ስለጨለማው ቁጭ ብለው አይነጫነጩም፣ ጨለማውን ብርሃን ያበሩበታል:: “ጨለማውን መቶ ጊዜ ከምትረግመው ይልቅ አንዲትን ሻማ ማብራት ይመረጣል” እደሚባለው ማለት ነው:: ይህንን አይነቱን ዝንባሌ ለማዳበር የሚከተሉት እይታዎች ይረዱሃል ብዬ አምናለሁ::

አመለካከትህንና አደራረግህን ለውጥ

ሁኔታዎች እንደጠበካቸው በማይሄዱበት ጊዜ መጀመሪያ ማጤን ያለብህ አመለካከትህንና አደራረግህን ነው:: ስኬታማ ሰዎችን ከስኬተ-ቢስ ሰዎች የሚለያቸው አንዱ ቁልፍ ሁኔታቸውን ለመለወጥ በቅድሚያ አመለካከታቸውን መለወጥ እንዳለባቸው ማወቃቸው ነው:: አንድ ችግር ውስጥ ስትገባ፣ ወደዚያ እንድትገባ ያደረገህ አመለካከት ካለ፣ በዚያው አመለካከት ችግሩን መቀልበስ አትችልም:: “አይቻልም” የሚለውን “ይቻላል” በሚለው፤ “በቃኝ” የሚለውን “አላቆምም” በሚለው፤ “ዋጋ ቢስ ነኝ” የሚለውን “ዋጋ ያለኝ ሰው ነኝ” በሚለው ካልተቀየረ ለውጥ አይመጣም:: ይህ የአመለካከት ለውጥ በተግባርህ ላይ ታላቅ የሆነ ተጽእኖ አለው:: አመለካከት ሲለወጥ አደራረግ ይለወጣል፣ አደራረግ ሲለወጥ ደግሞ ሁኔታ ይለወጣል:: ብዙ ሰዎች ያንኑ አስተሳሰባቸውን ይዘው ሁኔታቸውን ግን ለመለወጥ ይፈልጋሉ:: ይህ በፍጹም የማይቻል ነገር ነው:: ለምሳሌ፣ የቆሸሸን ከተማ ንጹህ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ በቅድሚያ ንጹህ አመለካከት በሕብረተሰቡ ውስጥ መፍጠር አስፈላጊ ነው:: አለዚያ፣ እውነታው የበራለት ሰው እያጸዳ የሄደውን አካባቢ ያልበራለት ሰው ኮቴውን ተከትሎ ያቆሸሸዋል::

“ልክ አመለካከትህ ሲለወጥ በዙሪያህ ያለው ነገር ሁሉ ከዚያው ጋር አብሎ ይለወጣል” - Steve Maraboli

የሰውን አመለካከት መለወጥ በዚህች ምድር ላይ እጅግ ከባድ ከሚባሉ ስራዎች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል:: ይህ የሆነበት ምክንያቱ እጅግ ብዙ ነው:: ነገሩን በአጭሩ ስናጤነው ግን ሰው መለወጥ የማይፈልግ ፍጥረት እንደሆነ ፈጥኖ ይገለጥልናል:: ሁኔታችንን ለመለወጥ ከመሞከር ይልቅ ያለንበትን ሁኔታ የመልመድና በዚያ ዙሪያ የሕይወትን ዘይቤ መገንባት ይቀልለናል:: አንዳንድ ጊዜ፣ “ይህ ሁኔታ ምነው በተለወጠ” ብለን በምናስበው ሁኔታ ላይ እንኳ የለውጥን እርምጃ ለመውሰድ ስንወላውል ራሳችንን

Scanned with CamScanner